በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የወልድያ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢ ሂሳብ፣

1. ዩኒቨርሲቲው ከሚመለከታቸው የተለያዩ ድርጅቶች እና ሰራተኞች መሰብሰበብ የነበረበትን የቅጣትና የኪራይ ገቢ በድምሩ ብር 2,853,542.37 ያልሰበሰበ መሆኑን፣

2. ዩኒቨርሲቲው ለኢትዮ ስታንዳርድ ፉድስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም፣ ብር 41,086.96 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ሳያደርግ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

3. የዩኒቨርስቲው ሹፌሮች ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሂደው በሚቆዩበት እና በሚያድሩበት ቀናት ከተመደበላቸው የአልጋ አበል በተጨማሪ ከውስጥ ገቢ በቀን ብር 100.00 ሂሳብ በድምሩ **ብር 73,100.00** ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱ፣
4. ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ከተተመው የቀን የምግብ ወጪ በላይ በድምሩ ብር 38,017.70 ከመመሪያ ውጭ በተጨማሪ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱን፣
5. ዩኒቨርስቲው የሚመለከተውን አካል ሳያስፈቅድ በድምሩ ብር 31,176.00 አለአግባብ ከመንግስት ደንብና መመሪያ ውጭ ጥቅማ ጥቅም ቶፕ አፕ በሚል ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
6. ዩኒቨርሲቲው በዋናው ግቢ ውስጥ ለጀመረው የከብት ማድለብ እና ለወተት ሀብት ልማት የገቢ ማመንጫ በሚሰበስበው ገቢ መሆን ሲገባው፣ በድምሩ ብር 394,782.29 ከደንብና መመሪያ ውጭ ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ መገኘቱን፣
7. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር **2,096,279.04** የዕቃ ግዥን እና የአገልግሎት ክፍያን አገልግሎቱ በተገኘበት በበጀት ዓመት መፈጸም ሲገባው፣ ከ2009 በጀት ዓመት ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣
8. ዩኒቨርስቲው ለመስተንግዶ ያለአግባብ ከውሉ ውጭ በተጨማሪ ብር 5,680.00 ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣
9. ዩኒቨርስቲው ለጥበቃ አገልግሎት በውሉ ላይ ከተቀመጠው እና ከተጠቀሱት ውጭ ስራ ላይ በሌሉ እና አገልግሎት ባልሰጡ ሰራተኞች ሥም በድምሩ **ብር 315,837.47** በተጨማሪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን፣
10. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር **294,581.03** ከተለያዩ አቅራቢዎች ላይ የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

11. ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ወጪዎችን በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በድምሩ ብር 420,693.75 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣
12. ዩኒቨርስቲው ለክፍያዎች በማስረጃነት መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ /Cash sale invoice/ መሆን ሲገባው፣ የብር **5,413,439.25** በተለያየ ቀን ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ ሲፈፅም የዱቤ የሽይጭ ደረሰኝ /Credit sale invoice/ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ በመቁጠር ሂሳቡ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑን፣
13. ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር **7,359,009.62** ላወጣው ወጪ የወጪ ደረሰኝ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣
14. ዩኒቨርስቲው ለተማሪዎች ለምግብ እና ለውሎ አበል ከተጠየቀዉ በላይ በብልጫ ብር 62,985.00 ያለአግባብ ክፍሎ መገኘቱን፣
15. ዩኒቨርሲቲው ብር 21,034.10 ለኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የጀኔሬተር መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም በአንድ ክፍያ ሁለት ጊዜ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) እና ቅድመ የገቢ ግብር (Withhold) ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍሎ መገኘቱን፣
16. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር **36,188,433.98** የተለያዩ ግዥዎች ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሳይቀርብ ከግዥ መመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣
17. ዩኒቨርሲቲው በብር 362,758.00 በግልጽ ጨረታ መግዛት ሲገባው፣ ከግዥ መመሪያው ውጭ በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣
18. ዩኒቨርሲቲው ለአሸናፊው ድርጅት ተወዳድሮ ባሸነፈበት ዋጋ መሰረት መክፈል ሲገባው፣ ከግዥ መመሪያ ውጭ ዋጋ በመጨመር ብር **194,175.00** በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱን፣
19. ዩኒቨርሲቲው የሙዚቃ መሳሪያ ግዥ ባወጣው ጨረታ አንድ ተጫራች ብቻ የቀረበ በመሆኑ በማለት ሁለተኛ ጨረታ ሳይወጣ ወይም የመንግስት ግዥና ንብ/አስ. ኤጀንሲን በማስፈቀድ እና የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ሳይገናዘብ በድምሩ በብር 2,612,931.10 ከቀረበው አንድ አስመጪ ተጫራች በቀጥታ ግዥውን ፈጽሞ መገኘቱን፣

20.ዩኒቨርሲቲው ከውሉ ስምምነት ውጭ ብር 883,610.70 የማጓጓዣ/የትራንስፖርት/ ተጨማሪ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

21.ዩኒቨርሲቲው ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፣ በድምሩ ብር 20,403,854.50 ከግዥ መመሪያ ውጭ ሙሉ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣

22.ዩኒቨርሲቲው ለግንባታ ስራ ሌላ ተጨማሪ ውል ሳይኖረው ብር 2,164,619.64 ከውሉ በላይ በብልጫ የከፈለ መሆኑን፣

23.ዩኒቨርሲቲው ድርጅቱ የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ ምክንያት በድምሩ ብር 17,724,599.13 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ ሳያደርግ ወይም ሳይቀንስ የተገኘ መሆኑን፣

24.ዩኒቨርሲቲው ለአገልግሎት ክፍያ በብልጫ ብር 960.00 ያለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

25.ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 39,710,505.52 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ የተገኘ መሆኑን፣

<u>በጀት፣</u>

26.ዩኒቨርሲቲው ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ብር **48,993,357.87** ከተደለደለው በጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 26 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት ዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ያለምንም ደንብ እና መመሪያ በድምሩ ብር 5,524,311.80 ለወልድያ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የ2008 እና የ2009 በጀት ዓመት የይዞታ /የቦታ /ክራይ በሚል ያለአግባብ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 71,430.00 የውሎ አበል ቅጾች ሳይሞሉና ሳይፈረሙ እንዲሁም ሰራተኞቹ በተባለው ቦታ የሄዱበትን ስራ በትክክል ሰርተው ለመምጣታቸው በሚመለከተው ኃላፊ ያልተረጋገጠ መሆኑ እና ገንዘቡ ለሰራተኞቹ ለመከፈሉ በፊርማቸው ያላረጋገጡ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ በጀት እና ከካፒታል በጀት በድምሩ ብር **59,644,766.67** ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣

ሌሎች ጉዳዮች፣

- በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ በንብረት ደንብና መመሪያ መሠረት ዕቃዎች በአግባቡ ያልተያዙና ያልተወገዱ እንዲሁም የተዘረጋ የንብረት ቁጥጥር ስዓርት ባለመኖሩ ለረዥም ጊዜ በመቀመጣቸው ለብክነት እየተዳረገ መሆኑን፣
- ዩኒቨርስቲው የተጠናቀቁ ግንባታዎች በዩኒቨርስቲው በቋሚ ንብረት ካርድ በሀብትነት መመዝገብ እንዳለባቸው ቢያዝም ያልተመዘገቡ መሆናቸው፣
- በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የወልድያ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በወልድያ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

የወልድያ ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለተሰበሰበ የቅጣትና የኪራይ ገቢ፣</u>

የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 4 የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ስለማድረግ የመንግስትን ገቢ በመሰብሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ማድረግ እንደሚገባ በመመሪያው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው፡-

- በግቢው የሚገኙትን ለንግድ እና ለመዝናኛ አገልግሎት የሚሆኑ ክፍሎችን ለተለያዩ ማህበራት በውል ያከራየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ውሉ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው በወሩ የመጨረሻ ቀን በዩኒቨርስቲው የሂሳብ ቁጥር በማስገባት ደረሰኙን ለዩኒቨርስቲው የፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ገቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን በየወሩ የሚከፈለውን ኪራይ እስከ ቀጣይ ወር አምስተኛ ቀን ድረስ ካልተከፈለ 10 በመቶ በመጨመር፣ እስከ አስረኛ ቀን ካልተከፈለ 25 በመቶ በመጨመር፣ እስከ አስራ አምስተኛው ቀን ድረስ ካልተከፈለ 50 በመቶ በመጨመር እና እስከ ወሩ መጨረሻ ካልተከፈለ 75 በመቶ በመጨመር ከነቅጣቱ ወርሃዊ ክፍያውን መክፈል እንዳለበት በውሉ የተገለፀ ቢሆንም፣ የፋይናንስ ክፍሉ ከሃይማኖት በዛብህ (የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ካፌ አገልግሎት) በ16/07/2009 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የአራት ወር (ከህዳር እስከ የካቲት ድረስ) ያለውን የኪራይ ክፍያ ብር 20,000.00 ገቢ ያደረጉ ሲሆን፣ በውሉ መሰረት ገቢ ባለማድረጋቸው ውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ቅጣት ሳይታሰብ ወርሃዊ ክፍያውን ብቻ ገቢ የተደረገ በመሆኑ ቀሪ ያልተሰበሰበ ከህዳር እስከ ጥር ላለው ክፍያ የቅጣት ብር 11,250.00 (3*5,000.00=15,000.00*75%) በተጨማሪም የየካቲት ወር ቅጣት 2,500.00 (5,000.00*50%) በድምሩ ብር 13,750.00

ወርሃዊ ክፍያው በወቅቱ ባለመከፈሉ የቅጣት ክፍያ መከፈል ሲገባ ያልተከፈለ መሆኑ፡፡

- በተጨማሪም ከኪራይ የሚገኘውን ወርሃዊ ክፍያ በውሉ መሰረት ተከታትሎ በአግባቡ መሰብሰብ ሲገባው በድምሩ ብር 129,596.25 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩን ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተሉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የማህበሩ ስም	በውሉ መሰረት ወረሃዊ የኪራይ ክፍያ መጠን በብር	በወሉ መሰረት ያልተከፈለባቸው ወራቶች ብዛት	ያልተከፈለ ክፍያ	በውሉ መሰረት ባለመከፈሉ ማህበሩ መቀጣት የነበረበት የገንዘብ መጠን	በጠቅላው ያልተከለ የገንዘብ መጠን
1	ሙሉጌታ ሰጠ (ጭማቂ ቤት)	1,890.00	የ2 ወር (መጋቢት እና ሰኔ)	2*1890.00 = 3,780.00	3,780.00*75 % = 2,835.00	6,615.00
2	እነ አስረበብ ሳራ እና ጓደኞቻቸው ካፌ እና ሬስቶራንት ህ/ሽ/ማ	3,000.00	የ2 ወር (መስከረም እና ሰኔ)	2*3,000.00 = 6,000.00	6,000.00*75 % = 4,500.00	10,500.00
3	ጌታቸው መላሹ (የፅህፈት አገልግሎት)	2,137.50	የ2 ወር (መስከረም እና ታህሳስ)	2*2,137.50 = 4,275.00	4,275.00*75 % = 3,206.25	7,481.25
4	ሂወት ፈንታው (የቴንስ እና ከረንቡላ አገልግሎት)	5,000.00	የ10 ወር (ከመስከረም እስከ ሰኔ)	10*5,000.0 = 50,000.00	50,0000.00* 75% = 37,500.00	87,500.00
5	ሃይማኖት በዛብህ (የመምህራንና የአስተዳደር	5,000.00	የ2 ወር (ጥቅምት እና ግንቦት)	2*5,000.00 = 10,000.00	10,000.00* 75% = 7,500.00	17,5000.00

	ሰራተኞች ካፌ አገልግ ሎት)					
	ድምር			77,946.00	58,459.50	129,596.25

- እንደዚሁም ለተቋሙ የህግ አገልግሎት የተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች ወደ ሚመለከተው የህግ አካል የቀረቡና ውሳኔ ካገኙ በኃላ የተወሰደ እርምጃ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣
    - የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የነበሩና ከተቋሙ ጋር ውል በመግባት ለትምህርት የተላኩ መምህራን በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ካልተወጡ መምህራን ውስጥ የ2 መምህራን መላኩ ማሞ እና ሳሙኤል ተገኝ በህዳር 01/2007 በብር 102,000.00፣ ክንዱ ወንድሙ በ10/03/2007 ብር 61,664.36፣ የ3 መምህራን ጀማል አሊ፣ ሃብታሙ ማሩ እና ገነት ሽፈራው በ07/02/2007 ብር 102,000.00፣ የ3 መምህራን በሃይሉ አበበ፣ አክሊሉ አዳነ እና አማረ ጌታቸው በ28/07/2007 ብር 90,787.50 በድምሩ ብር **356,451.86** ሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰራተኞቹ እንዲከፍሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም እስከ አሁን ገቢ ያልሆነ መሆኑን፣
    - ዮሴፍ ተከተል ህንጻ ተቋራጭ የግንባታ ስራውን አቋርጦ በመጥፋቱ በተመሰረተበት ክስ በ29/02/2009 ብር 2,853,744.26 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቋራጩ እንዲከፍል ብይን የሰጠ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 500,000.00 የከፈለ ሲሆን ቀሪው ብር 2,353,744.26 ያልተከፈለ መሆኑን፣

በጠቅላላው ብር **2,853,542.37** ዩኒቨርሲቲው እስከ አሁን ድረስ ገንዘቡን ከሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ከድርጅቶቹ ገቢ ያላደረገ /ያላስመለሰ/ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 ስጋት፣

- መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ በስራ ላይ የዋለውን የመንግስት መመሪያ ሊጥስ ይችላል፡፡
- በፍርድ ውሳኔ እንዲከፍሉ ከተወሰነባቸው ሰራተኞች ላይ ወዲያውኑ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ ለግለሰቦች መጠቀሚያ ሆኖ እንዲቀርና ወደ ማይሰበሰብበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሳይሰበሰብ የቀረው የኪራይ ገቢ ተሰብስቦ ለዩኒቨርስቲው ገቢ ሊደረግና በፍርድ ውሳኔ ያገኘ የመንግሥትም ገንዘብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተሰብስቦ ገቢ እንዲሆን የሥራ አመራሩ እርምጃ በመውሰድ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

- የሰራኞች መዝናኛ አገልግሎት ከሚሰጡ ክፍሎች መካከል ለወ/ሮ ሃይማኖት በዛብህ የያዙት የመምህራንና ሰራኞች ካፌ ኪራይ በተመለከተ ቀደም ሲል ይሰሩበት የነበረውን የመዝናኛ ቦታ ለቀው ተጫርተው ወደ አሸነፉበት አዲሱ ክበብ ሲዛወሩ ቁሳቁሶች ያልተሟሉለት ስለነበርና ስራ ለማስጀመር የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ ክፍያ ሊቀነስልኝ ይገባል ብለው በማመልከታቸው እና ለቀረበው ጥያቄም ቶሎ ምላሽ ባለመሰጠቱ የ4 ወር ጊዜ በመውሰዱ ክፍያ ሳይፈጽሙ ሲሰሩ ቆይተዋ፡፡

  በኋላም ማኔጅሜንቱ ምን ያህል መክፈል እንዳለባቸው የወሰነላቸውን ክፍያ ከነጉዳት ካሳው ማስከፈሉ ተገቢ አለመሆኑን እና በዩኒቨርሲቲው ችግር ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን የግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማብራሪያ በመስጠቱና ጉዳዩ በበላይ አመራሩ የታመነበት ስለነበር ያለቅጣት እንዲከፍሉ አድርገናል፡፡ ከዚህም በላይ ዋናው የዩኒቨርሲቲው ትኩረት በተደጋጋሚ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቦርድ፣ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለሌሎች አካላት በመምህራንና ሠራተኞች ሲቀርብ የነበረው የምግብና የመዝናኛ አቅርቦት ችግር

በመሆኑና ክበቡን በማከራዬት ገቢ ማስገባት ሳይሆን ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሠራተኞች የምግብና የመጠጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ በመሆኑና ይህንንም አገልግሎት በተጥናከረ መንገድ እየሰጡልን በመሆኑ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ ያመዘነ ስለነበረ ቅጣት ማስከፈሉ ትክክለኛ ነው ተብሎ አልታመነም።

- የውል ግዴታቸውን ባልተወጡ መምህራን ላይ በድምሩ 356,451.86 ብር እንዲከፍሉ የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ብይን ቢሰጥም የመምህራኑ አድራሻ እስካሁን ሊገኝ ባለመቻሉ በህግ አገልግሎቱ በኩል የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- የዮሴፍ ተከተል የህንጻ ስራ ተቋራጭ ፍ/ቤት የወሰነበትን ክፍያ በመጀመሪያው ዙር ብር 500,000.00 ገቢ መደረጉን እና በኋላም ተጨማሪ ክፍያ በመክፈል በአሁን ወቅት ክፍያው ብር 1,700,000.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪውን ደግሞ ክትትል እየተደረገ እንዲመልስ እየሆነ ነው፡፡

1.2.1 <u>ግኝት፡ ያልተቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 13 እና14 በቅድመ የገቢ ግብር እና በክፍያ ላይ የሚከፈልን የተጨማሪ እሴት ታክስ በገዢው ላይ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም በወጣው መመሪያ መሠረት ተቀናሽ መደረጉን ኦዲት ሲደርግ፣ ዩኒቨርሲቲው ለኢትዮ ስታንዳርድ ፉድስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 14/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916411 ለመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ከተከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 41,086.96 (315,000.00 ÷1.15*15%) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ሳይደርግ ክፍያውን ለማህበሩ የፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል።

1.2.2 <u>ስጋት፤</u>

ማናቸውም ክፍያ ከአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥ ክፍያ ሲከናወን መቀነስ ያለበት ግብር አለመሰብሰቡ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ስርዓት ሊጎዳ ይችላል፡፡

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማዕከሉ ከዕቃ እና ከአገልግሎት ግዥ ሳይሰበስብ የቀራውን ግብር በመሰብሰብ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለመንግስት ገቢ መደረግ ያለበት ታክስ በትክክል አገልግሎቱን ከሰጠዉ ማህበር ተመላሽ ተደርጎ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከኢትዮ ስታንዳርድ ፋድስ ቫት ያልተቆረጠበት ምክንያት ድርጅቱ አገልግሎቱን ሲሰጠን ገና ስራ እየጀመረ ስለነበር የቫት መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያላሳተመና የእፎይታ ጊዜው ያላለፈ በመሆኑ ነው፡፡

2 <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

2.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከመመሪያ ውጭ ለመኝታ አበል ተከፍሎ የተገኘ፣</u>

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ መደብና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ መሆኑንና ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር/ሲሰሚ/30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/2003 ከደንብና መመሪያ ውጭ እየተከፈሉ ያሉ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአስቸኳይ እንዲቋረጡ መመሪያ የተላለፈ መሆኑ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የዩኒቨርስቲው ሹፌሮች ለዩኒቨርስቲዉ ስራ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሄደዉ በሚቆዩበት እና በሚያድሩበት ቀናት ከተመደበላቸዉ የአልጋ አበል በተጨማሪ ከውስጥ ገቢ በጀት ላይ በቀን 100 ብር ሂሳብ ለ18 ሾፌሮች ለ731 ቀናት በድምሩ ብር 73,100.00 ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተሉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የሠራተኛዉ ስም	የወጪ ማስመከሪያ ቁ.	የተከፈለበት ቀን	የቀን ብዛት	የተከፈለው ብር
1	ሃ/ማሪያም አበበ	683922	27/11/08	3	300.00
		195734	05/08/09	15	1,500.00
2	መሀመድ አወል	195666	21/06/09	17	1,700.00
		195843	12/10/09	25	2,500.00

ተ.ቁ	የሠራተኛዉ ስም	የወጪ ማስመከሪያ ቁ.	የተከፈለበት ቀን	የቀን ብዛት	የተከፈለው ብር
3	ቢኒያም ሳምሶን	684118	14/04/09	19	1,900.00
		195868	22/10/09	21	2,100.00
4	ተ/ሚካኤል አድማሱ	683933	04/12/08	19	1,900.00
		436769	25/11/08	22	2,200.00
		195712	19/07/09	17	1,700.00
		195838	07/10/09	20	2,000.00
		195786	07/09/09	15	1,500.00
5	ወንድወሰን ፈንታዉ	195680	29/06/09	18	1,800.00
		0163941	06/06/09	19	1,900.00
		436784	11/01/09	21	2,100.00
6	ጋሻዉ ምህረቱ	0163950	08/06/09	18	1,800.00
		684108	12/04/09	20	2,000.00
7	አሊ ጌታሁን	684124	18/04/09	19	1,900.00
		195742	10/08/09	16	1,600.00
		195678	28/06/09	24	2,400.00
8	ሰኢድ አህመድ	436883	10/05/09	55	5,500.00
		195707	15/07/09	23	2,300.00
		195655	13/06/09	22	2,200.00
		436797	18/02/09	31	3,100.00
9	ተስፋየ አሰፋ	195860	20/10/09	15	1,500.00
		0163931	30/05/09	16	1,600.00
		195738	10/08/09	18	1,800.00
10	ሰይድ ይማም	195802	16/09/09	15	1,500.00
		684146	03/05/09	15	1,500.00
11	ዘላለም አምባዉ	195743	10/08/09	22	2,200.00
		0163948	07/06/09	15	1,500.00
13	አራጋው በቀለ	195846	14/10/09	18	1,800.00
		195670	22/06/09	16	1,600.00
14	ተስፋየ ያለለት	195735	05/08/09	18	1,800.00
15	አበበ እንዳየነ	195732	04/08/09	19	1,900.00
16	ተስፋየ ሙልየ	195832	05/10/09	17	1,700.00
17	በሬ ካሳሁን	195795	11/09/09	15	1,500.00
18	ሙሉጌታ ይመር	195834	06/10/09	18	1,800.00
		195668	22/06/09	15	1,500.00
	ጠቅላላ ድምር			731	73,100.00

2.1.2 ***ስጋት፣***

- *መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡*
- *የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡*
- *ከህግ እና መመሪያ ውጭ የሆኑ ውሳኔዎችን በመስጠት የሚከፈል ሂሳብ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡*

2.1.3 ***የማሻሻያ ሀሳብ፣***

ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.1.4 ***የስራ አመራሩ ምላሽ፣***

የዩኒቨርሲቲው አንጻና ዋናዉ ችግሩ ከሾፌሮች ጋር የተያያዘ ሲሆን ሹፌሮቹ አዘውትረው የሚጓጓዙ ከመሆኑ አንጻርና ይዘዋቸው የሚሄዱት የመንግስት ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው በመሆናቸውና ከሚከፈላቸው አበል አንፃር ከፍለው የሚያሳድሩባቸው ቦታዎች እጦት በመኖሩ እና ችግር ውስጥ እየገቡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በየእለቱ የመልካም አስተዳደር ችግር ተደርጎ እየቀረበ በመሄዱ ማኔጅመነቱም ችግሩን አጥንቶ ሾፌሮቹ በተመደበላቸው ገንዘብ አልጋ ይዘው የሚያድሩባቸው ሆቴሎች እጅግ ዝቅተኛ የሆኑ በመሆናቸው መኪኖቹን ይዘው ለመሄድና ለማሳደር ችግር እየገጠማቸው መሆኑን ተገነዝቧል፡፡ ስለሆነም ችግሩን ተመልክቶ የማኔጅመንት ካውንስሉ ከውስጥ ገቢ ድጎማ እንዲደረግላቸው በመወሰንና በቦርድ እንዲፀድቅ በማስደረግ በተቻለ መጠን ግቢ ያላቸው መኝታ ቤቶች እንዲያድሩና የመኪኖች ደህንነት እንዲጠበቅ ተደርጓል። ይህም ሁኔታ የሹፌሮችን የሁልጊዜ እሮሮ በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ምንም እንኳ ችግሩን ለመፍታት የተወሰደው እርምጃ ከፍተኛ ወጭ ወጥቶባቸው የተገዙትን መኪኖች ደህንነት ለማስጠበቅ ያስቻለና ቦርድም የተሰጠውን ስልጣን መሰረት አድርጎ የተወሰደ ቢሆንም በተደጋጋሚ የኦዲት ግኝት ተደርጎ በመቅረቡ ከሐምሌ 2009 ዓ/ም ጀምሮ ግን በተሰጠን አስተያየት መሰረት ክፍያው እንዲቆም ተደርጓል፡፡

2.2.1 ግኝት፣ ለተማሪዎች ከተተመነው የምግብ ወጪ በላይ ክፍያ መፈጸሙን፣

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ሃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 1.ሀ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመስሪያ ቤታቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና የፀደቀውን በጀት መሰረት በማድረግ ወጪዎችን በመፈፀም በኩል መስሪያ ቤታቸውን የመምራትና የመወከል ፕሮግራሞችንና መስሪያ ቤታቸውን የሚመለከቱ ህጎች በማስፈፀም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት ወጪ ኦዲት ሲደርግ፣ በ15/05/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438843 የሲቪል ምህንድስና፣ የውሃ ሀብት እና መስኖ ምህንድስና፣ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ተማሪዎች በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቤት-ሙከራ ትምህርት ለመማር ለሚሄዱ ለ45 ተማሪዎች የቀን የምግብ ወጪያቸው በብር 19.50 ሂሳብ ለ12 ቀን ብር 10,530.00፣ ለ761 ተማሪዎች የቀን የምግብ ወጪያቸው በብር 19.50 ሂሳብ ለ7 ቀን ብር 103,876.5 በድምሩ ብር 114,406.50፣ የማኔጅመንት ክፍያ ለተማሪዎቹ የሚከፈላቸው ጠቅላላ የምግብ ክፍያ 20% ብር 22,881.30 (114,406.50*20%)፣ እንዲሁም የዕቃ እርጂና(ዲፕሪሴሽን) ክፍያ ለተማሪዎቹ የሚከፈላቸው ጠቅላላ የምግብ ክፍያ እና የማኔጅመንት ክፍያ ድምር 20% ብር 27,457.56 (114,406.50+22,881.30)* 20% በሚል በድምሩ ብር 164,744.90 ለባህርዳር ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ክፍያ የከፈለ ሲሆን፣ ክፍያው መንግስት ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ ሲወጡ እንዲከፈላቸው በወሰነው የቀን የምግብ ወጪ ብር 15.00 ሂሳብ ቢሆን ኖሮ ብር 88,005.00 የምግብ ወጪ (45*12*15=8,100)+(761*7*15=79,905)፣ የማኔጅመንት ክፍያ ለተማሪዎቹ የሚከፈላቸው ጠቅላላ የምግብ ክፍያ 20% ብር 17,601.00 (88,005.00*20%)፣ እንዲሁም የዕቃ እርጅና (ዲፕሪሴሽን) ክፍያ ለተማሪዎቹ የሚከፈላቸው ጠቅላላ የምግብ ክፍያ እና የማኔጅመንት ክፍያ ድምር 20% ብር 21,121.20 (88,005.00+17,601.00)* 20% በጠቅላላው ብር 126,727.20 መከፈል ሲገባው ያለአግባብ ብር 38,017.70 ከመመሪያ ውጭ በተጨማሪ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

ከመንግስት የክፍያ መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈፀም ለሌሎች ብልሹ አሰራሮች በር ሊከፍት ይችላል፡፡ እንዲሁም መንግስትን ያላግባብ ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል ፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመንግስት መመሪያ ውጭ ያላግባብ የመንግስትን ገንዘብ ለተግባር ልምምድ ለወጡ ተማሪዎች ክፍያ እንዲከፈላቸው ያዘዘው አካል ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ እና ለወደፊቱም እንደዚህ ያለ አሰራር እዳንይኖር የመንግስት ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈፀም ይገባል፡፡

2.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት ብቃትና ተወዳዳሪነት ያላቸው ተማሪዎችን ለማፍራት በተገቢው መንገድ ማሰልጠን በመሆኑ ይህንን ለማሳካት ደግሞ በግቢው ውስጥ የቤተ ሙከራ ክፍል ባለመኖሩ ምክንያት በቂ እውቀት ያገኙበታል ብለን ወደ አሰብነው ወደ መከላከያ ኢንጅነሪንግ ዩኒቨርሲቲ ወስደናቸዋል፡፡ ለተማሪዎቹ ከመንግስት የተመደበላቸው የምግብ ክፍያ በቀን 15.00 ብር ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው የተመደበውን በጀት ሳይሆን ለአንድ ተማሪ ብር 19.50 ክፍያ በመጠየቁ ይህንን ክፍለን ተማሪዎቹ ማግኘት የሚገባቸውን እውቀት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ትምህርቱን በወቅቱ ማጠናቀቅ ስለማይችሉ የግድ አንድ ሴሚስተር እንዲጨምሩ ስለሚገደዱና ከዚም በኋላም ቢሆን እንዳማረጭ የምንወስድበት ሌላ ተቋም ባለመኖሩ የተማሪዎችን የመመረቂያ ጊዜ ከማራዘሙ በተጨማሪ መንግስትን ለከፍተኛ ወጭ ሊዳርገው እንደሚችል በመገንዘብ የተፈፀመ ነው፡፡

2.3.1 ግኝት፣ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም፣

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች የደመወዝ መጠንና ጥቅማ ጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ የተደነገገ መሆኑን እና ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር/ሲሰሚ/30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/2003 ከደንብና መመሪያ ወጭ

እየተከፈሉ ያሉ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአስቸኳይ እንዲቋረጡ መመሪያ ተላልፏል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ አቶ ምናየ ገበየሁ በምክትል ስራ አስኪያጅነት ደረጃ ላይ ሆነው እንዲሰሩና በሚያገኙት እና በምክትል ስራ አስከያጅነት መደብ የተተከለውን የደመወዝ ልዩነት እንደቶፕአፕ ከሰኔ 01/2006 ዓም ጀምሮ እንዲከፈላቸው የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በቁጥር ወዩ/1352/01-ፕ/06 ባሳወቀው መሰረት የ2009 በጀት ዓመት ከሐምሌ/2008 እስከ ሰኔ/2009 ድርስ በየወሩ ብር 2,598.00 ሂሳብ የ12 ወር ብር 31,176.00 ከህግና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.3.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግስት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ውጭ በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድም ሆነ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተለያዩ ውሳኔዎችን ሲሰጡ መንግስት የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ግንባታው ተፋጥኖ ተማሪዎችን ተቀብሎ የመማመር ማስተማሩን ሂደት ለማስቀጠል ፕሮጀክቱን በጽ/ቤት ደረጃ የሚሰተባብርና ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ አስፈላጊ ስለነበር ሀላፊ የሚሆን ባለሙያ ለመቅጠር በተደጋጋሚ ማስታወቂያ ቢወጣም ለቦታው በተቀመጠው አነስተኛ ደመወዝ ሊመጣ የቻለ አንድም ተወዳዳሪ ባለመገኘቱ አማራጭ መውሰድ አሰፈላጊ ነበር፡፡ በዚህ መሰረትም በባለሙያነት ተቀጥረው እየሰሩ

ከነበሩት ሁለት ባለሙያዎች መካከል የተሻለ የስራ ልምድ እና የስራ አፈፃፀም የነበረው አቶ ምናየ ስራውን ደርቦ ይዞ እንዲሰራ ቢደረግም የስራ ጫናው እየበዛበት መሄዱን በመግለጽ ውክልናው እንዲነሳለት በተደጋጋሚ በመጠየቁ የዩኒቨርሲቲው አመራር ችግሩን ለመፍታት ቢሞክርም ምንም መፍትሄ ለማግኘት ባለመቻሉ ጉዳዩን ለቦርድ አቅርቦ ቦርዱም ችግሩ ከፍተኛ መሆኑንና ግንባታውም በታቀደለት አኳኋን ለመሄድ የሚያስችል ባለመሆኑ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለባለሙያው ከደመወዙ ላይ ጥቅማ ጥቅም በመጨመር ስራው ሳይስተጓጎል እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅት የም/ስራ አስኪያጅነት መደብን መስፈርት አሟልቶ በመገኘቱና ምደባ የተሰጠው በመሆኑ ጥቅማ ጥቅሙን በማቆም ደመወዙን ብቻ እንዲያገኝ በማድርግ የተሰጠው አስተያዬት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

2.4.1 <u>ግኝት፣ ከመደበኛ በጀት ለውስጥ ገቢ ማመንጫ የተከፈለ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል:: የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለፌዴራል መንግስት የፋይናስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ክፍል ሦስት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በዋናው ግቢ ውስጥ ለጀመረው የከብት ማድለብ እና ለወተት ሀብት ልማት ለሚያስፈልጉ ለተቀነባበረ የከብቶች መኖ ግዥ ብር 350,548.29፣ ለከብቶች መድኃኒት ግዥ ብር 28,034.00፣ ለመኖና መድኃኒት ማጓጓዣ ብር 13,500.00 እና የማስጫኛና ማውረጃ ብር 2,700.00 ወጪ ያደረገ ሲሆን ወጪው የሚሸፈነው የገቢ

ማመንጫው በሚሰበስበው ገቢ መሆን ሲገባ፣ ከደንብና መመሪያ ውጭ በድምሩ ብር 394,782.29 ከመደበኛ በጀት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የከብቶች መኖ እና የከብቶች መድሀኒት ግዥው ከመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ የተገዛ ግዥ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.4.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ወጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

2.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

አለአግባብ ከመደበኛ በጀት ለውስጥ ገቢ ማመንጫ ወጪ የተደረገው ገንዘብ ወደ መደበኛው ሂሳብ ተመላሽ ሆኖ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በተሰጠው አሰተያየት መሰረት የተጠቀሰው ገንዘብ ወደ መደበኛ በጀት በቀጠዩ ሩብ አመት ፈሰስ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2.5.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ያለበጀት ዓመቱ የተከፈለ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሠረት የበጀት ዓመት ከሐምሌ1----ሰኔ 30 መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በ18/11/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438013 ብር 291,663.75 ለተድላ ጓንጉል የማገዶ እንጨት አቅርቦት በ2008 በጀት ዓመት ገቢ ላደረጉት፣

- በ13/12/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438081 ብር 39,406.13 ለጤና ባለሙያዎች በሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣
- በ13/12/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 83955 ብር 228,695.00 በ2008 ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ለሴት ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ላስተማሩ ለ104 መምህራን የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣
- በ25/01/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438690 ብር 951,480.26 ለዛምና ኤክስፐረስ ኢንተርናሽናል የስፖርት እቃዎችን በ2008 ዓ.ም ስላቀረቡ የተከፈለ ክፍያ፣
- በ05/03/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 436854 ብር 709,160.00 በኤክስቴንሽን፣ ማታ እና የክረምት መርሃ ግብር ለተሳተፉ ሃላፊዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች ከተከፈለዉ ክፍያ ዉስጥ ብር 266,160.00 በ2007 ዓ.ም ለተሳተፉ ሃላፊዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች የተከፈለ፣
- በ12/12/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438967 ብር 318,873.90 ለተወበ ፈንታ (ላል ሆቴል) በ2008 በጀት ዓመት ለተጠቀሙበት የመስተንግዶ ክፍያ፣

በድምሩ ብር **2,096,279.04** የዕቃ ግዥን እና የአገልግሎት ክፍያን አገልግሎቱ በተገኘበት በበጀት ዓመት መክፈል ሲገባው፣ ከ2009 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.5.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስትን በጀት ከደንብና መመሪያ ወጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በላይ የሒሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎችን ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡

2.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ የበጀት ዓመቱን ግዢ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ እና በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ቀደም ሲል በተሰጠን የማሻሻያ ሃሳብ የእርምት እርምጃ ወስደናል፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ በዚህ ዓመት እንደተፈጠረውና ሌሎች ምክንያቶች የዓመቱ የትምህርት ጊዜ ከሰኔ 30 በኋላ የሚጠናቀቅበት ሁኔታ ስለሚኖር እና ለመማር ማስተማሩ ሰራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችና የተማሪዎች የምግብ ግብዓቶች ስለሚቀርቡ የተፈጠረው አይነት ሁኔታዎቹ ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲያዝ እንገልፃለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ አቅራቢዎች እቃዎችን በጊዚያዊ መረካከቢያ ቅጽ ካስረከቡ በኋላ ጥለው ስለሚጠፉና ጊዜ አሳልፈው ክፍያ ስለሚጠይቁ የዚህ ዓይነት ሁኔታ አልፎ አልፎ ይከሰታል፡፡ ሆኖም በተቻለ መጠን ችግሩን ለማስወገድ የሚቻለንን ሁሉ ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን።

2.6.1 <u>ግኝት፣ ያለአግባብ ወጪ የተደረገ የመስተንግዶ ክፍያ፣</u>

ለመስተንግዶ አገልግሎት ወጪ የሆኑ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከአስ/ል/ም/ፕሬዚዳንት ለግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በቁጥር ወዩ/2642/03-አስ/08 በቀን 04/13/08 በተፃፈ ደብዳቤ ለቦርድ አባላት የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲመቻችላቸው መታዘዙ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በ16/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439069 ወጪ ከተደረገው ገንዘብ ውስጥ ከታዘዘው ውጭ በተጨማሪ ለአቶ ንዋይ ወርቁ የ8 ቀን የአልጋ ክፍያ ለ1 አልጋ በብር 530.00 ሂሳብ መሰረት 8*530.00 = ብር 4,240.00 ያለአግባብ ወጪ ተደርጎ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣
- በ22/07/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916438 ለአያት ሮሃ ሆቴል ለ61 ሰው ለ2 ቀን ለ1 አልጋ በብር 480.00 ሂሳብ መሰረት የተዋዋለ ሲሆን፣

የተከፈለው ግን ከውሉ ውጭ በተጨማሪ የ3 አልጋ ለአንድ ቀን 3*480.00 = ብር 1,440.00 የከፈለ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 5,680.00 ያለአግባብ ከውሉ ውጭ በተጨማሪ መከፈሉን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.6.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ለብልሹ አሰራር በር ሊከፈት ይችላል፡፡

2.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ (ሳይታዘዝ) ወጭ የተደረገዉ ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊትም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.6.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

አገልግሎቱን ካገኙ ሰራተኞቸ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ትእዛዝ ተላልፏል፡፡ ክትትልም እየተደረገ ነው።

2.7.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከውሉ ውጭ ተከፍሎ የተገኘ፣</u>

ዩኒቨርስቲው የተለያዩ ውሎችን ሲዋዋል እና ክፍያ ሲፈፅም በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በወልድያ ዩኒቨርስቲና በህዳሴው ፍሬ የጥበቃ ህብረት ስራ ማህበር መካከል ለወልድያ ዩኒቨርስቲ ጀነቶ በር ግቢ የጥበቃ ስራ ለ2009 ዓ.ም አገልግሎት ለመስጠት የዉል ስምምነት መደረጉ ይታወቃል፡፡ በስምምነቱ በቁጥር 8 የአገልግሎት ሰጭ ግዴታ በሚለዉ ስር 8.3 ላይ ማህበሩ ለአገልግሎቱ ብቁ የሆነ የሰዉ ሃይል 156 ሠራተኞችን የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በግለፅ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም 8.4 ላይ አገልግሎት ሰጭው የሚያሰማራቸው ሰራተኞች የብቃት ማነስ ችግር ቢኖርባቸዉ በ10 ቀናት ዉስጥ ብቃት ባላቸው ሰራተኞች የመቀየር ግዴታ አለበት፡፡ በተጨማሪም በቁጥር 11 ስለ ክፍያ አፈፃፀም ላይ 11.3 አገልግሎት ሰጭ ለሰጠው አገልግሎት ዋጋ በወሩ ዉስጥ ተገኝተዉ ስራ በሰሩት የጥበቃ አባል ቁጥር ውል በገባው መሰረት በየወሩ ይከፍላል፡፡ ክፍያዉ

የሚፈፀመውም ውል የተገባባቸዉ በሙሉ የሰሩ መሆኑ በቢሮ አገልግሎት ሃላፊዉ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን በውሉ ላይ ከተቀመጠው እና ከተጠቀሱት ውጭ ስራ ላይ በሌሉ እና አገልግሎት ባልሰጡ ሰራተኞች ሥም በድምሩ ብር 315,837.47 ወጪ ሆኖ መከፈሉን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የባንክ ወጪ ቁጥር	ወጪ የሆነ በት ቀን	በስራ ለይ የተገኙ ሰራተኞች ብዛት	ዉሉ ላይ በአንድ ሰዉ የሚከፈል ገንዘብ	የተከፈለ ገንዘብ	መከፈል የነበረበት	በብልጫ የተከፈለ
1	916173	07/07/09	118	1,518.44	236,877.03	179,175.92	57,701.11
2	916235	08/07/09	118	1,518.44	236,877.03	179,175.92	57,701.11
3	916308	25/08/09	115	1,518.44	236,877.03	174,620.60	62,256.43
4	917077	29/09/09	112	1,518.44	236,877.03	170,065.28	66,811.75
5	917202	30/10/09	109	1,518.44	236,877.03	165,509.96	71,367.07
ጠቅላላ ድምር					1,184,385.15	868,547.68	315,837.47

2.7.2 <u>ስጋት፣</u>

- በመመሪያ መሰረት ክፍያ ካልተፈፀመ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- የውሉን ታማኝነት እና ተፈፃሚነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

2.7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ ክፍያ ሊፈፀም ስለሚገባ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ ሊደረጉ እና ለወደፊትም ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.7.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በወቅቱ የጥበቃ ሰራተኞች ቁጥር ያልተሟላ ቢሆንም ማህበሩ በእረፍት ላይ ያሉትን አባላት በእረፍት ጊዚያቸው ገብተው እንዲሰሩ እና የተጓደሉቱን ሰዎች ቦታ ሸፍነው እንዲሰሩ በመደረጉ ከዩኒርሲቲው ጋር በገቡት ውል መሰረት ዩኒቨርሲቲው የሚጠብቅባቸውን የጥበቃ አገልግሎት ያለምንም መሸራረፍ የሰጡ መሆኑ ተረጋግጦ ክፍያው ለማህበሩ እንዲፈፀም የተደረገ መሆኑን እየገለጽን ጉዳዩ በተደጋጋሚ በማህበሩና በዩኒቨርሲቲው በኩል ውይይት ተደርጎበት መተማመን ላይ የተደረሰበት

በመሆኑ ሥራውን ሸፍነው ለሚሰሩ አባላት መከፈል ያለበት በመሆኑና አባላቱም በነጻ ሊሰሩ የሚገደዱበት ሁኔታ ባለመኖሩ ሥራው በተፈለገው የሰው ኃይል እየተሸፈነ መሆኑ በዩኒቨርሲቲው እየተረጋገጠ ክፍያው እንዲከፈል ሆኗል። ሆኖም የአባላቱ ቁጥር በተባለው መጠን እንዲሟላ ከማህበሩ፣ ከከተማ አስተዳደሩና ከዞኑ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ስምምነት ላይ ተደርሷል። በአሁኑ ወቅትም የተባሉት አባላት ተሟልተዋል።

2.8.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ የተገኘ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሰረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን ባያስረክብ (ሀ) አቅራቢ ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በ30/06/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916385 ብር 686,996.20 ለመሃመድ ሰኢድ ጀነራል ትሬዲንግ የወለል ምንጣፍ የተከፈለው በተገባው ውል መሰረት እስከ ጥር 25/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 0093920 ገቢ የተደረገው በየካቲት 10/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 15 ቀን 686,996.20*1/1000*15 =10,304.94 የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በ29/07/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439432 ብር 10,710,230.60 ከኦሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ የምግብ ቤት ዕቃዎች ግዢ በውል መሰረት እስከ ታህሳስ 29/2009 ድረስ ማስገባት ሲገባው ንብረቱን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ቁጥር 0093833 ገቢ የተደረገው በጥር 26/2009 በመሆኑ ማስገባት ሲገባው ላዘገየበት 26 ቀን 10,710,230.60*1/1000*26=278,466.00 የጉዳት ካሳ መቀነስ ሲገባው አቅራቢው የይራዘምልኝ ጥያቄ ያቀረበበት ማስረጃ እና በዚሁ መሰረት የማናጅመንት ኮሚቴ የቀረበውን የይራዘምልኝ ጥያቄ

አግባብነት በማየት ይሁንታውን የተቀበለበት የቃለ-ጉባዔ ማስረጃ ሳይኖር በግዥ ዳይሬክተሩ ብቻ በተጻፈ ደብዳቤ ሙሉ ክፍያ የተከፈለው መሆኑ፣

- በ08/09/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916573 በብር 528,190.00 የስፖርት ዕቃዎች ከድርጅቱ የገዛ ሲሆን አቅራቢው በውሉ መሰረት ገቢ እንዲያደርግ የተሰጠው ቀነ ገደብ እስከ የካቲት 20/2009 ዓ.ም ሲሆን ዕቃው ለዩኒቨርስቲው ገቢ የሆነው በቀን 01/07/09 በመሆኑ አቅራቢው በውሉ መሰረት ባለማቅረቡ ላዘገየበት የ11 ቀን የጉዳት ካሳ (11*1/1000*528,190.00) ብር 5,810.09 መክፈል ሲገባው ሙሉ ክፍያ የተከፈለው መሆኑን፣

በጠቅላላ ብር 294,581.03 የጉዳት ካሳ ከአቅራቢዎች ላይ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

2.8.2 <u>ስጋት፣</u>

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ገቢ እንዲያደርጉ ካልተደረገ ዩኒቨርሲቲው ከገዛው ዕቃ ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም በስራ አፈጻጻሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

2.8.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው አቅራቢው (ድርጅቱ) እንዲከፍል በማድረግ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለገንዝብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ካላቀረቡ የጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ማድረግ ወይም ያስያዙት ሲፒኦ ሊወርስ ይገባል።

2.8.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ለመሃመድ ሰኢድ ጀነራል ትሬዲንግ የተከፈለ የወለል ምንጣፍ የጉዳት ካሳ ብር 10304.34 ያልተከፈለው ቀሪ ክፍያ ስላለው ተቀናሽ እንዲደረግ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ትእዛዝ ተላልፏል።
- ለኦሚዳድ የተሰጠው የጊዜ ማረዘሚያ በዳይሬክተሩ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም የተባለው በተመለከተ በወቅቱ በነበረው አሰራር የማራዘሚያ ጊዜ የሚሰጠው አመልካቾቹ ሲያመለክት ጉዳዩ በማኔጅመንት ካውንስል በጋራ ይታይና ውሳኔ

ከተሰጠበት በኋላ የግዥ ዳይሬክተሩ ደብዳቤ ጽፎ እንዲያራዝምላቸው ይደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ የማያስኬድ ከሆነ ወደፊት የሚሻሻል ይሆናል። በሌላ በኩል ድርጅቱ እቃዎቹ ማስረከብ ከሚገባበት ጊዜ ቀድሞ ቢያመጣም የቴክኒክ ገምጋሚው ባለሙያው ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ የሚመጡ በመሆናቸውና በወቅቱ በነበረባቸው ችግር የተነሳ በቦታው ተገንተው እቃውን አረጋግጠው ገቢ ለማድረግ ባለመቻሉን የተፈጠረ ችግር ነው፡፡

- የየስፖርት አቅራቢ ድርጅቱ የስፖርት እቃዎቹን በወቅቱ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ተደርጎ ሞዴል ባይቆረጥለትም የዩኒቨርሲቲው ቴክኒክ ኮሚቴ በነበረበት የስራ ጫና ምክንያት እቃዎችን በወቅቱ ማረጋገጥ ባለመቻሉ በጊዚያዊ የንብረት ርክክብ ቬርቫል ገቢ የተደረገ በመሆኑ እና የአቅራቢም ችግር ባለመሆኑ የጉዳት ካሳ አልተቆረጠም፡፡

2.9.1 <u>ግኝት፣ በብልጫ የተከፈለ የአገልግሎት ክፍያ፣</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 *ክፍል* 2 *አንቀፅ* 9 *ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ንዑስ አንቀፅ* 4 *ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊ ሲሆን ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርሲቲዉ* በ03/04/09 *በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር* 439526 *ለበትዕግሰት መስተንግዶ ህብረት ስራ ማህበር የህዳር ወር* 2009 *ዓ.ም የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ብር* 290,176.27 *መከፈል እንዳለበት ያረጋገጡ ሲሆን፣ እንደዚሁም ከማህበሩም ይኸው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የተቆረጠ ሲሆን፣ የተከፈለው ክፍያ ግን ብር* 291,136.27 *በመሆኑ በብልጫ ብር* **960.00** *ያለአግባብ መከፈሉን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

2.9.2 <u>ስጋት፣</u>

ከህግ እና *መመሪያ ዉጭ የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል፡፡*

2.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለዉ ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

2.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በየካቲት ወር 2010 ዓ/ም ከሚከፈላቸው የአገልግሎት ክፍያ ላይ ተመላሽ እንዲደረግ በተሰብሳቢ ተይዟል፡፡

2.10.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪ□ ቁ□ር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተራ ቁጥር 3 የሂሳብ አወቃቀር ስርአት በሚለው ስር የመንግስት መስሪያ ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በ18/11/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438013 ለተድላ ጓንጉል ብር 291,663.75 የማገዶ እንጨት ክፍያ የከፈለ ሲሆን ወጪውን በሂሳብ መደብ 6218 /ለሌሎች አቅርቦቶች/ በሚል መመዝገብ ሲገባ በሂሳብ መደብ 6257 /ለመብራት/ በሚለው የተመዘገበ መሆኑን እና በተጨማሪም የማገዶ እንጨት ግዥው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና የወጪ ደረሰኝ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ያልቀረበ መሆኑን ታውቋል፡፡
- በ01/13/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439008 ብር 129,030.00 ለሶሎዳ የንፅህ እና የወረቀት ውጤቶች ማምረቻ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ለሶፍት ግዥ ክፍያ ሲፈፅም በ6218 ለሌሎች አቅርቦቶች መመዝገብ ሲገባዉ 6231 በውሎ አበል የተመዘገበ እና በትክክለኛው የሂሳብ መደብ በ6218 ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ በብር **472,633.97** ከበጀት በላይ መሆኑን የሚያመላክት ስለመሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በድምሩ ብር 420,693.75 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2.10.2 ስጋት፣

ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም የተፈቀደ በጀት በማለቁ ምክንያት ሆን ተብሎ የተፈጸመ ሊሆን ይችላል፡፡ ለፈፀመው ክፍያ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡

2.10.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደባቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ የፋይናንስ ክፍሉ ማናቸውንም ክፍያዎች ከመፈጸሙ በፊት ለሚከፈሉ ክፍያዎች ማስረጃ /ማወራረጃ /ሊሆኑ የሚችሉ ህጋዊ ደረሰኞችን ሰነዱ ጋር መያያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግና ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

2.10.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ከዚህ ቀደም በ2008 በመጡት ኦዲተሮች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የምዝገባ ማስተካከያ ተደርጎለታል፡፡

2.10.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ከዚህ ቀደም በ2008 በመጡት ኦዲተሮች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የምዝገባ ማስተካከያ ተደርጎለታል ተብሎ ምላሽ የተሰጠው ግኝቱ የተገኘው በ2009 በጀት ዓመት በመሆኑ ምንም ዓይነት ማስተካከያ ያልተደርገ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.11.1 ግኝት፣ በዱቤ የሽይጭ ደረሰኝ /Credit sale invoice/ የተወራረደ ሂሳብ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም የአገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው ለክፍያዎች በማስረጃነት መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ /Cash sale invoice/ መሆን ሲገባው፣ የብር **5,413,439.25** በተለያየ ቀን ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ ሲፈፅም የዱቤ የሽይጭ ደረሰኝ /Credit sale invoice/ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ በመቁጠር ሂሳቡ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የባንክ ወጪ ማስመሰያ ቁጥር	የእቃው አቅራቢ ድርጂት ስም	የወጪው ምክ ንያት	የተከፈለው የገንዘብ ልክ
1	09/05/09	438833	ለአበርገሌ አለም አቀፍ የእንስሳት ሀብት ልማት ኃ/የተ/የግ/ማ/	ለስጋ አቅርቦት ክፍያ	513,218.00
2	22/05/09	438857	ለቦኤዝ የምግብ ኮምፕልክስ ኃ/የተ/የግ/ማ/	ለፓስታ ግዥ	370,000.00
3	15/05/09	438840	ለእድገት ልብስ ስፌት ኃ/የተ/የግ/ማ/	የደንብ ልብስ ግዥ	488,692.50
4	30/06/09	916378	ለቦኤዝ ምግብኮ ምፕልክስ ኃ/የተ/የግ/ማ/	ለፓስታ ግዥ	370,000.00
5	01/13/08	439009	ለብሪጅቴክ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/	ሲ.ዲ ግዥ	20,260.70
6	03/13/08	438109	ለብሪጅቴክ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ	ላፕ ቶፕ ኮምፒ ዩተር ግዥ	1,284,935.25
7	19/08/09	916518	ለከንዓን ዱቄት ፋብሪካ	የዳቦ ዱቄት ግዥ	481,466.70
8	08/09/09	916581	ለከንዓን ዱቄት ፋብሪካ	የዳቦ ዱቄት ግዥ	772,586.10
9	30/05/09	438892	ለየካቲት የወረቀት ስራዎች ድርጅት	የኮምፒዩተር ወረቀት ግዥ	983,250.00

ተ.ቁ	ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስያ ቁጥር	የእቃው አቅራቢ ድርጂት ስም	የወጪው ምክ ንያት	የተከፈለው የገንዘብ ልክ
10	01/13/08	439008	ለሶሎዳ የንፅህና እና የወ ረቀት ውጤቶች ማምረቻ	የሶፍት ወረቀት ግዢ	129,030.00
ድምር					**5,413,439.25**

2.11.2 **ስጋት፣**

የመንግሥትን ህግና ደንብ ሳይከተሉ የሚሰሩ አቅራቢዎችን የሚያበረታታ ሲሆን አቅራቢዎቹ ገቢያቸውን እንዲደብቁና የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ እንዳይከፍሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

2.11.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ሂሳቡ በወጪ ሊመዘገብ የሚገባው ህጋዊ የሽያጭ ደረሰኝ ሲቀርብለት በመሆኑ የሽያጭ ደረሰኙ ሊቀርብ ይገባል። ለወደፊቱም ወጪዎች ህጋዊ ደረሰኝ ሲቀርብላቸው ብቻ መመዝገብ ይኖርባቸዋል::

2.11.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

- በገጽ 19 ላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ በተገለጸው መሰረት በተራ ቁጥር 1 &7 እና 8 ከተጠቀሱት ድርጅቶች ደረሰኝ ሰብስበን እያይዘናል፡፡
- በተራ ቁጥር 2 እና 4 ስሙ የተጠቀሰው ድርጅት ለሙሉ ክፍያ እንጅ ቫትና ዊዝሆልዲንግ ለተቆረጠበት አልሰጥም በማለቱ ጉዳዩ ለጉሙሩክና ገቢዎች ባለስልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ የምናስታውቅ ይሆናል፡፡
- በተራ ቁ. 5,6,9 እና 10 ደረሰኝ ሰብስበን የምናያይዝ ይሆናል።

2.12.1 **ግኝት፣ የወጪ ማስረጃ የሌለው፣**

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 እና በፌዴራል መንግሰት የሂሳብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለማንኛውም ወጪ ክፍያ መፈጸም የሚገባው ተመጣጣኝ የክፍያ ደረሰኝ በማስረጃነት ሲቀርብ ብቻ

እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 7,359,009.62 ላወጣው ወጪ ማስረጃ/ደረሰኝ/ የሌለው መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የባንክወጪ ማስመስያ ቁጥር	የእቃው አቅራቢ ድርጂት ስም	የወጪው ምክንያት	የተከፈለው የገንዘብ ልክ
1	28/06/09	916360	ለጀምበር ሁለገብ የገበሬዎች ህ/ስ/ማህበር ዩኒየን	ለጤፍ ግዥ	3,340,000.00
2	15/05/09	438844	ለባህር ዳርዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	ለተግባር ትምህርት ክፍያ	654,033.60
3	15/05/06	438843	ለባህር ዳርዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	ለተግባር ትምህርት ክፍያ	291,663.75
4	29/06/09	916369	ለኢትዮጵያከፍ/ትም/ተቋማት ተማ/ህብረት	ዓመታዊ መዋጮ	10,000.00
5	04/05/09	438824	ለጂማ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርትማህበር	የአባልነት ክፍያ	10,000.00
6	23/03/09	438725	ለወልድያ ጠ/ሆስፒታል	የተማሪዎች ህክምና ክፍያ	19,946.80
7	22/10/09	916735	ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	አመታዊ መዋጮ	200,000.00
8	22/10/09	916737	ለኤስ ኦ ኤስ	ድጋፍ	199,000.00
9	10/08/09	916489	ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	ለአገር አቀፍ የማትማትክስ ኮንፍረንስ ድጋፍ	30.000.00
10	23/10/09	096015	ለወልድያ ከተማ አስተዳደር ከተማ አገልግሎትፅ/ቤት	የቦታ ክራይ ክፍያ	2,524,311.80
11	02/13/08	439020	ለፓልርዮስ ልጆቹ (ኢትዮጵያ) ሊሚትድ	የተሽከርካሪ ጥገና ክፍያ	80,053.67
				ድምር	**7,359,009.62**

2.12.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርስቲው ለፈፀመው ክፍያ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡ አቅራቢዎቹ ገቢያቸውን እንዲደብቁና የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ እንዳይከፍሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

2.12.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውንም ክፍያዎች ከመክፈሉ በፊት ማስረጃ/ማወራረጃ /ሊሆኑ የሚችሉ ህጋዊ ደረሰኞችን ክፍያው ከተፈፀመላቸው አካሎች በመቀበል ከክፍያ ሰነዱ ጋር መያያዙን በማረጋገጥ ክፍያ ሊከፈል ስለሚገባ ከሚመለከተው አካል ማስረጃውን በማስመጣት ከወጪው ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

2.12.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ተራ ቁ 1, 10 እና 11 ደረሰኝ ተያይዛል፡፡
- ተራ ቁ 2, 3, 4, 5, 7 እና 9 ደረሰኝ ለመስጠት ፈቃደኝ ባለመሆናቸው ማያያዝ አልተቻለም። ጉዳዩንም ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ነን።
- የወልዲያ ሆስፒታል በክልሉ የፋይናንስ አሰራር መሰረት ደረሰኝ እንዲሰጥ ስለማያስገድድና በክሬዲት ኢንቮይስ ምዝገባ ስለሚያከናውኑ ደረሰኙን መያያዝ አልቻልንም፡፡

2.12.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ተራ ቁ 1, 10 እና 11 ደረሰኝ ተያይዛል ተብሎ ምላሽ የተሰጠው ከተላከልን መልስ ጋር ምንም ዓይነት ደረሰኝ የተያያዘ የለም፡፡ በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2.13.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከተጠየቀዉ በላይ የተከፈለ የምግብ እና የዉሎ አበል ክፍያ፣</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ንዑስ አንቀፅ 4 ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊ ሲሆን ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ

ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ዩኒቨርስቲዉ በቀን 28/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ 916454 የ3ኛ ዓመት መደበኛ ሚድዋይፈሪ ትምርት ክፍል ተማሪዎች ለተግባር ትምህርት ወደ አላማጣ ጠቅላላ ሆስፒታል እና ለምለም ካርል ሆስፒታል(ማይጨዉ) ሲሄዱ በቀን 18/07/09 ዓ.ም የጤና ሳይንስ ፋካሊቲ ለአስ/ተማ/አገ/ም/ፕ/ጽ/ቤት ለ35 ተማሪዎች የመጓጓዣ ቀናትን ጨምሮ የ57 ቀን የምግብ እና ውሎ አበል ሁሉም ካፌ ተጠቃሚዎች በመሆናቸዉ በቀን 65 ብር (35*57*65=129,675.00) እንዲከፈላቸዉ ተጠይቆ በ19/07/09 ዓ.ም የአስ/ተማ/አገ/ም/ፕ/ጽ/ቤት በቀረበዉ ጥያቄ መሰረት እንዲፈፀም ለፋይናንስ እና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተመርቶ ሳለ የተከፈለው ግን ከቀረበው ጥያቄ ውጭ ለ52 ተማሪዎች በቀን 65 ብር (52*57*65=192,660.00) ሲሆን በብልጫ ብር 62,985.00 ያለአግባብ መከፈሉን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.13.2 <u>ስጋት፣</u>

- የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- ከህግ እና መመሪያ ዉጭ የሆኑ ዉሳኔዎችን በመወሰን የሚከፈል ክፍያ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡

2.13.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለዉ ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

2.13.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተሰጠውን አስተያየት መሰረት በማድረግ በተሰብሳቢ ተይዞ ከተማሪዎቹ እየተቀነሰ ይገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ 28,750.00 ብር እንዲሰበብ ተደርጓል፡፡ ቀሪውም ተሰብስቦ እንዲመለስ ይደረጋል።

2.14.1 <u>ግኝት፣ የውሎ አበል ቅጾች ሳይሞሉና ሳይፈረሙ የተፈጸመ ክፍያ፤</u>

በኢፌድሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 2004 ዓ.ም ስለመንግስት ሰራተኞች የቀን የውሎ አበል አከፋፈል የወጣ መመሪያ ክፍል 3 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚለው ስር ስለ ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅጾች ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የውሎ አበል መጠየቂያ ፣መፍቀጃ እና መክፈያ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባላቸው ሰራተኞች ወይም የስራ ሃላፊዎች እንዲሞሉ ያደርጋል ይላል፡፡ በዚህ መሰረት የውሎ አበል ክፍያዎችን አግባብነት ለማጣራት ኦዲት ስናከናውን ዩኒቨርሲቲው ለ28 ሰራተኞች በድምሩ ብር 71,430.00 የከፈለ መሆኑን በቀረበው በማስረጃ ቢገለጽም ሰራተኞቹ በተባለው ቦታ የሄዱበትን ስራ በትክክል ሰርተው ለመምጣታቸው በሚመለከተው ኃላፊ ያልተረጋገጠ መሆኑ እና ገንዘቡ ለሰራተኞቹ ለመከፈሉ በፊርማቸው ያላረጋገጡ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.14.2 <u>ስጋት፤</u>

ተገቢው ማስረጃ አለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም በተጨማሪም የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.14.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ሰራተኞቹ በትክክል ስራውን ሰርተው ለመምጣታቸው ስራውን እንዲሰሩ የላካቸው አካል ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ሰራተኞቹ በትክክል ውሎ አበል ለመቀበላቸው በውሎ አበል ፎረሙ ላይ በፊርማቸው ማረጋገጥ አለበቸው ካልሆነም ገንዘቡ ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

2.14.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

መምህራኑ የመስክ መልስ ሪፖርት እንዲያያዙ ለክፍሎቻቸው በደብዳቤ ታዟል፣

2.15.1 ግኝት፣ ሁለት ጊዜ የታክስ እና ግብር ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 13 እና14 በቅድመ የገቢ ግብር እና በክፍያ ላይ የሚከፈልን የተጨማሪ እሴት ታክስ በገገርው ላይ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም በወጣው መመሪያ መሠረት ተቀናሽ መደረጉን ኦዲት ስናደርግ፣ ዩኒቨርሲቲው በቀን 01/13/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439007 ብር 21,034.10 ለኢካቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የጀኔሬተር መለዋወጫ እቃዎች ግዥ ክፍያ ሲፈፀም በአንድ ክፍያ ሁለት ጊዜ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) እና ቅድመ የገቢ ግብር (Withhold) ከመመሪያ ውጭ መከፈሉን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል።

2.15.2 ስጋት፣

ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበት የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ገቢ ላይደረግ ይችላል፡፡ እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

2.15.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለመንግስት ገቢ መደረግ ያለበት ታክስ በትክክል አገልግሎቱን ከሰጠዉ ማህበር ተመላሽ ተደርጎ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ሁለት ጊዜ ወጪ የተደረገዉ ገንዘብ አንደኛዉ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ዩኒቨርሲቲው የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.15.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ምላሽ አልተሰጠበትም፡፡

2.16.1 ግኝት፣ ያለ አግባብ የተከፈለ የቦታ/ የይዞታ/ግብር ክፍያ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 3 ‹‹ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግስት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግስትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር

ወይም ቀረጥ የማስከፈል ስልጣን አይኖራቸውም፡፡›› ተብሎ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የወልዲያ ዩኒቨርሲቲም መንግስት በነደፈው ከፍተኛ ትምህርትን የማስፋፋት እቅድ መሰረት ከከፈታቸው አዳዲስ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሲሆን ስራውን በ2004 ዓ.ም ሲጀምር መንግስት የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራትና ማህረሰብ አቀፍ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሆን በሚል የሚገለገልበትን መሬት በነፃ የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ ግልፅ ባልሆነ እና መከፈል ሳይገባዉ በቀን 14/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916191 ብር 1,500,000.00፣ በቀን 02/05/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439594 ብር 1,500,000.00፣ በቀን 23/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 096015 ብር 2,524,311.80፣ በድምሩ ብር **5,524,311.80** ለወልድያ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የ2008 እና የ2009 በጀት ዓመት የይዞታ /የቦታ /ክራይ በሚል ያለአግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል።

2.16.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስት ገንዘብ ያለ አግባብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

2.16.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

መንግስት የተማረ የሰዉ ሃይል ለማፍራትና ማህረሰብ አቀፍ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሆን በሚል የሚገለገልበትን መሬት በነፃ የተሰጠ በመሆኑ የቦታ ኪራይ መክፈል ስለማይገባ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.16.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለወልዲያ ከተማ የ2008 እና 2009 የተከፈለ ዩኒቨርሲቲው የሚገለገልበት የቦታ ኪራይ ክፍያ ከተማ አስተዳደሩ የማስከፈል መብት አለኝ በማለት ከክልሉ ስራና ከተማ ልማት የተሰጠውን ደብዳቤ በማያያዝ የተከፈለ መሆኑ እየገለፅን የተሰጠውን አስተያት መሰረት በማድረግ የ2010 ዓ/ም ክፍያ ያልፈጸምን መሆኑን እንገልጻለን፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን ጥያቄው በከተማ አስተዳደሩ እየቀረበ ከመሆኑ ባሻገር

የባንክ አካውንታችን እንደሚያዘጉብን እያሳሰቡን ስለሆነ የክልል እና የፌደራል መ/ቤቶች ሊኖራቸው በሚገባ የግንኙነት ሁኔታ አንጻር ህጋዊ መፍትሄ እንዲሰጥበት እንጠይቃለን፡፡

2.17.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ያለውድድር የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው አንቀጽ 15 የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ንዑስ አንቀጽ 15.1 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና የግዥ መመሪያ አንቀጽ 4/ሀ ላይ የመንግስት ግዥ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በግዥ አፈጻጸም ረገድ በውድድር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ማስገኘት ስለሆነ አስፈላጊውን የገበያ ጥናት ተደርጎ ወይም የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ተንተርሶ ሊሆን እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ-6 አንቀጽ-52 ተራ ቁጥር አንድ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል-ሀ. ዕቃው፣ ግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ከሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፡-

- በ19/12/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438980 ብር 57,000.00፤ በ03/02/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439144 ብር 125,303.00 እና በ29/09/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 917076 ብር 49,250.00፣ በድምሩ የብር **231,553.00** የጥገና አገልግሎት ግዥ ከአቶ ፊንታቢል ሞላ የገዛ መሆኑን፣
- በ06/03/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 84040 ብር **84,294.02** የእንጨት ግዥ ከአቶ ሞላ ጌታሁን የገዛ መሆኑን፣

- በ01/13/08 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439007 የብር 142,289.50 የጀነሬተር መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ከኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የገዛ መሆኑን፣
- በ30/10/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 917212 የብር 180,889.00 የጥገና አገልግሎት ከኦሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የገዛ መሆኑን፣
- በ11/02/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438631 የብር 335,800.00፤ በ03/08/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916468 የብር 496,800.00 እና በ02/09/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916559 የብር 402,960.00 በድምሩ የብር 1,235,560.00 የቀለም ግዥ ከኦሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የገዛ መሆኑን፣
- በተለያዩ ቀናት ከተለያዩ ዘጠኝ ሆቴሎች እና ሬስቶራንቶች የብር 2,019,324.08 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣
- በተለያዩ ቀናት ከተለያዩ አምስት ካምፓኒዎች የብር 1,686,641.56 የተሽከርካሪዎች የጥገና እና ሰርቪስ አገልግሎት እና ከሁለት ድርጅቶች የብር 70,624.00 የተሽከርካሪ ጌጣጌጥና ዕቃ ግዥ በድምሩ ብር **1,757,265.56** የፈጸመ መሆኑን፣
- በ24/02/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 83996 ለሁሴን አህመድና ልጆቹ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የብር 60,000.00 የዳቦ ሊጥ መቁረጫ /ክራንቻ/ ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣
- በ04/02/09 ከእነ እንዳሻውና ጓደኞቹ የጋቢዮን ህብረት ሽርክና ማህበር ጋር የጋቢዮን ስራ ለማሰራት በብር 1,608,981.10 ያለ ውድድር በቀጥታ ውል ያሰረ ሲሆን በ29/06/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439383 ብር **603,387.00** የከፈለ መሆኑን፣
- በ04/02/09 ከአባይ ነውና ጓደኞቹ የጋቢዮን ህብረት ሽርክና ማህበር ጋር የጋቢዮን ስራ ለማሰራት በብር 1,528,140.92 ያለ ውድድር በቀጥታ ውል

ያሰረ ሲሆን በ28/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439332 ብር **817,981.78** የከፈለ መሆኑን፣

- በ04/02/09 ከአረጋ ሞገስ የጋቢዮን ስራ የግል ኢንተርፕራይዝ ጋር የጋቢዮን ስራ ለማሰራት በብር 1,874,191.31 ያለ ውድድር በቀጥታ ውል ያሰረ ሲሆን በ28/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439330 ብር **880,463.94** የከፈለ መሆኑን፣
- ለምግብ ቤት አገልግሎት የሚውል የዳቦ መጋገሪያ ፓትራ ግዥ ከአሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ በቀን 09/06/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438922 ብር 213,717.50 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣
- የውስጥ ለውስጥ መንገድ የድንጋይ ንጣፍ ስራ እስከ 6ኛ ውለታ የመጀመሪያው ዙር ክፍያ ድረስ ብር 4,847,358.39 በ12 የክፍያ ማስረጃዎች ለመቻል ኮብልስቶን ንጣፍ ህ/ሽ/ማህበር ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፤
- በ23/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439246 ብር 4,945,741.50 ለተማሪዎች አገልግሎት የሚዉል ተደራራቢ አልጋ እና አርምቸር ከወልድያ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ግዥ መፈፀሙን፣
- ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የአገልግሎት ማለትም የጥበቃ ስራ፣ የወጥ ስራ፣ የእንጀራ መጋገር፣ መስተንግዶ፣ እና የፅዳት ግዥዎችን በድምሩ ብር 18,168,608.71 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣

በጠቅላላ የብር **36,188,433.98** የተለያዩ የግዥ አገልግሎቶች የሚገኙት ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ማወዳደር የማይቻል ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሳይቀርብ ከግዥ መመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.17.2 <u>ስጋት፤</u>

- በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም፡፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

- የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ባለመደረጉ ዩኒቨርሲቲው ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.17.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲያከናዉን የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ካልተቻለም ከሚመለከተው አካል አገልግሎቱን ለመግዛት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ መመሪያን የተከተለ ግዥ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.17.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

- ከቡሌት1-11 ለተጠቀሰው በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አሰተያየት መሰረት እንፈጽማለን፡፡
- የዳቦ መጋገሪያ ፓትራ ለመግዛት ለተለያዩ ድርጅቶች ፕሮፎርማ ቢበተንም ከኦሚዳድ ውጭ በወቅቱ ምላሽ የሰጠን ባለማግኘታችን እና ለተማሪዎቹ ዳቦ ከከተማው ያቀርብ የነበረው አቅራቢ እያዋጣኝም በሚል ከፍተኛ ዋጋ ከመጨመሩ ባሻገር በከተማው ውስጥ ካለው ከፈተኛ የመብራት መቆራረጥ ጋር አያዞ ለማቅረብ ባለመፈለጉና የከተማውን አስተዳደር እገዛ ብንጠይቅም ስላልተሰካልንና ችግር ውስጥ በመግባታችን በራሳችን ዳቦ ማቅረብ የግድ ስለነበረብን ጉዳዩ ለማኔጅሜንት ካውንስሉ ቀርቦ ለተበትነው ፕሮፎርማ ምላሽ ከሰጠው ድርጅት /ኦሚዳድ/ በአስቸኳይ ግዥው እንዲፈጽም የማነጅሜንት ካውንስሉ በወሰነው መሰረት ግዥ ተፈጽሟል።
- የአርም ቸር እና ተደራራቢ አልጋ በተመለከተ ግልጽ ጨረታ የወጣ ቢሆንም የጨረታው ሂደት ቅሬታ የቀረበበት በመሆኑ የመንግስት ግዥና ንብረት አሰተዳደር ኤጀንሲ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ ዩኒቨርሲቲውን መረጃ ሳይጠይቅ ጨረታው እንዲሰረዝ በማድረጉ እና ወቅቱም ተማሪዎችን የምንቀበልበት ጊዜ ስለነበር በደብደቤ የችግሩን አሳሳቢነት ለኤጀንሲው በጠየቅነው መሰረት የሰጠንን ምላሽ ይዘን በአፋጣኝ

ግብአቱን ለማሟላት በመመሪያው መሰረት ለትርፍ ካልተቋቋመ የመንግስት ድርጅት ግዥው እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት አንዱ አላማ ለአካቢው ነዋሪ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ሲሆን በጥቃቅን የተደራጁት ከአረብ ተመላሽና ስራ አጥ ወጣቶች የስራ እድል እንዲያገኙ የከተማ አስተዳደሩ በማህበር እያደራጀ የሶስትዮሽ ውል በመውሰድ በተለያዩ ዘርፎች አገልገሎት እያገኘን ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ማህበራትን አወዳድሮ ለማስገባትም ማህበራቱ በተቋቋሙበት አገልግሎት አይነት የከተማ አስተዳደሩ ያሉትን እያወዳደረ እንዲሰጠን በየጊዜው በደብደቤ በመጠየቅ በከተማውም ያሉት ማህበራት እነዚሁ መሆናቸውን መሰረት በማድረግ ለማወዳደር ባለመቻሉ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አካሄድ የከተማ አስተዳደሩ ማረጋገጫ እየሰጠ፣ እያደራጀና ዋስትና እየወሰደ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ እስካሁንም በሥራው ላይ መልካም አፈጻጸም ያላቸው በመሆኑ ለተማሪዎቻችን ጥሩ አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን።
- ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ለአካባቢው ህብረተሰብ ወይም ወጣቶች የተለያየ የስራ እድል መፍጠር እንዳለበት ይታወቃል። ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በወቅቱ በጌጠኛ ድንጋይ ወይም ኮብልስቶን ሊያሰራቸው ያሰበውን የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በስራ ዘርፉ ሰልጥነው ለተደራጁና ስራ ለሌላቸው ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ዞኑ ያሉትን አወዳድሮ እንዲልክልን ተጠይቆ መርጦ በላከልን መሰረት ተቀብለን ወደስራ እንዲገቡ ተደርጓል። በዚህ መሰረት የማህበሩን የስራ አፈጻጸም እንቅስቃሴ በመገምገም እንዲቀጥሉ ሆኗል። የውስጥ ለውስጥ መንገድ የድንጋይ ንጣፍ ስራ እስከ ስድስተኛ ውሉ የመጀመሪያው ዙር ክፍያ ድረስ ብር 4,847,358.39 በ12 የክፍያ ማስረጃዎች ለመቻል ኮብልስቶን ንጣፍ ህ/ሽርክና ማህበር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

2.18.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከመመሪያ ውጭ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣</u>

የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም በተሻሻለዉ አንቀጽ 24.2 መሰረት ለሌሎች አገልግሎት ግዥ ከብር 150,000.00 የማይበልጡ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ እንዲገዛ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲዉ በቀን 30/05/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439669 በብር 362,758.00 ከሎጎ ሃይቅ ደረጃ አንድ አነስተኛ መለ/የህዝብ ማመላለሻ ማህበር በ2009 ዓ.ም ለተማሪዎች ለተግባር ትምርት ወደ ተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚሄዱ እና ለግቢዉ ሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽረከርካሪዎችን ኪራይ ግዢ ሲፈፅም ከላይ የተጠቀዉን መመሪያ ያለአግባብ በመተላለፍ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.18.2 <u>ስጋት፣</u>

አስፈላጊነታቸዉ በመንግስት ታምኖበት በተለያየ ጊዜ የሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡

2.18.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲዉ የተለያዩ ግዥዎችን ሲፈፀም መንግስት በየጊዜዉ በሚያወጣቸዉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይከተሰት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.18.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አሰተያየት መሰረት እንፈጽማለን፣ ለ2010 በጀት አመት የአካባቢ ግልጽ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

2.19.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከግዥ መመሪያ ውጭ ዋጋ በመጨመር የተገዛ፣</u>

በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 5 አንቀፅ 24 በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥን አፈጻፀምን በተመለከተ በንዑስ አንቀፅ 24.4 ላይ ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በመንግስት መ/ቤቱ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም አይነት ድርድር ሊደረግ እንደማይችል ይገልፃል፡፡

በንዑስ አንቀፅ 24.11 ላይ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ /ፕሮፎርማ/ እና መ/ቤቱ ለአቅራቢው የግዥ ትእዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል እንደማያስፈልግ በመመሪያው የተቀመጠ ቢሆንም፤ ዩኒቨርስቲው ለተማሪዎች ምግብ የሚሆን የጤፍ ግዥን በዋጋ ማወዳደሪያ ከሁለገብ የገበያ ህብረት ስራ ዩኒየኖች እንዲገዛ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ድርጅት በቀን 29/02/2008 በደብዳቤ ቁጥር ወዩ/መግኤ/011/2/947 ስለፈቀደልን በማለት በቀን 03/12/08 በተያዘ ቃለጉባኤ በዋጋ ማቅረቢያ ተወዳደሪዎችን በማወዳደር ሞጣ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ዩኒየን አንዱን ኩንታል ጤፍ የትራንስፖርቱን፣ የመጫኛና ማውረጃውን ጨምሮ በብር 1,585.00 ያሸነፈ ስለሆነ ግዥው ከዚሁ ዩኒየን እንዲፈፀም በማለት የግዥ አወዳደሪ ኮሚቴዎች ለዩኒቨርስቲው ማኔጅመንት አቅርበዋል፡፡ ዩኒቨርስቲውም በቀን 06/12/08 በደብዳቤ ቁጥር ወዩ/1605/12-አስ/2008 ለሞጣ ሁለገብ ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን በፃፈው የግዥ ትዕዛዝ ደብዳቤ አቅርቦቱን ተወዳድሮ ባሸነፈበት ዋጋ አንዱን ኩንታል በብር 1,585.00 ሂሳብ እንዲያቀርብ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን በቀን 30/01/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 438601 የብር 7,033,450.00 ክፍያ ፈጽሟል፡፡ ይሁንና ዩኒቨርሲቲው የገዛው ጤፍ ብዛት 4315 ሲሆን አንዱን ኩንታል በብር 1,585.00 ሂሳብ (4315 * 1,585.00=ብር 6,839,275.00 በውድድሩ ባሸነፈበት ዋጋ መክፈል ሲገባው የከፈለው ብር 7,033,450.00 በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ለአሸናፊው ድርጅት ለ4315 ኩንታል ጤፍ አንዱን ኩንታል በብር 1,630.00 ሂሳብ ተጨማሪ በአንድ ኩንታል ብር 45.00 ከግዥ መመሪያ ውጭ ዋጋ በመጨመር ክፍያ መፈጸሙ ታውቋል። በዚህ መሰረት (7,033,450.00-6,839,275.00) ብር **194,175.00** ዩኒቨርሲቲው ለድርጅቱ በውድድሩ መሰረት ካሸነፈበት ዋጋ በላይ በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል። በተጨማሪም ንብረቱ በ11 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ከ20/12/08 እስከ 06/01/09 ተጠቃሎ ወደ ዩኒቨርሲቲው መጋዘን ከገባ በኋላ

ማናጅመንት ካውንስሉ የግዢውን ውሳኔ ክፍያው ከተፈጸመ በኃላ በ24/01/09 ያስተላለፈ መሆኑ ታውቋል።

2.19.2 ስጋት፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም፡፡ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ የመንግሥትም ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.19.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም ግዥዎች በፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያና ደንብ መሰረት እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.19.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የጤፍ ግዥው ከሞጣ ዩኔን ግዥ የተፈጸመበት ምክንያት ከፕሮፎርማ በኋላ በሰጡት ዋጋ ለመሸጥ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና በዩኒርሲቲው በወቅቱ ምንም አይነት የጤፍ ክምችት የሌለው በመሆኑ ለተማሪዎቹ የሚቀርብ የምግብ አቅርቦት ቢቋረጥ ከፍተኛ ሁከትና ብጥብጥ የሚያስከትል በመሆኑና ዋጋ ቢጨምሩም ከነሱ ጋር የተወዳደሩ ማህበራት አንጻር የተሻለ በመሆኑ ግዥው ተፈጽሟል፡፡ ሆኖም ችግሩን ለማስወገድ በ2010 ዓ/ም ግልጽ ጨረታ በማውጣት የጤፍ ግዥው ሂደት እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

2.20.1 ግኝት፣ አንድ ተጫራች በመቅረቡ ብቻ ከሱ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው አንቀጽ 15 የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ንዑስ አንቀጽ 15.1 በአዋጅና በመመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና የግዥ መመሪያ አንቀጽ 4/ሀ ላይ የመንግስት ግዥ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በግዥ አፈጻጸም ረገድ በውድድር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ማስገኘት ስለሆነ አስፈላጊውን የገበያ ጥናት ተደርጎ ወይም የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ተንተርሶ ሊሆን እንደሚገባ

ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የሙዚቃ መሳሪያ ግዥ ባወጣው ጨረታ አንድ ተጫራች ብቻ የቀረበ በመሆኑ በማለት ሁለተኛ ጨረታ ሳይወጣ ወይም የሚመለከተውን አካል ማለትም የመንግስት ግዥና ንብ/አስ/ኤጀንሲን በማስፈቀድ ባሉት የግዥ ዘዴዎች መጠቀም ሲቻል እና የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ዋጋን ሳይገናዘብ በ30/08/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 916331 ብር 1,696,491.50 እና በ17/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 917150 ብር 916,439.60 በድምሩ በብር **2,612,931.10** ከቀረበው አንድ ተጫራች ከሃፍቶም መንግስትአብ ታረቀ አስመጪ በቀጥታ ግዥውን ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.20.2 **ስጋት፣**

አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.20.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት አይችልም፣ ይህም የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጽም፣ በመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.20.4 **የስራ አመራሩ ምላሽ፣**

- የሙዚቃ መሳሪያ ግዥ ለመፈጸም በተደጋጋሚ ጨረታ የወጣ ሲሆን በመጀመሪያ የጨረታ ቁጥር ወዩ/ግ/ጨ/ቁ/04/2007 ጨረታ ወጥቶ አንድ ተጫራች ብቻ በመገኘቱ በድጋሜ የጨረታ ቁጥር ወዩ/ግ/ጨ/ቁ/05/2008 በወጣ ጨረታ ላይ አሁንም አንድ ድርጅት ብቻ የቀረበ በመሆኑ በወቅቱ ኮሚቴ በማቋቋም እና የገበያ ጥናት በማድረግ የተፈፀመ ግዥ ነው፡፡

2.21.1 <u>ግኝት፣ ከውሉ ስምምነት ውጭ የተከፈለ የማጓጓዣ/የትራንስፖርት/ ክፍያ፣</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 አንቀጽ 16(13) የጨረታ ቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) እና በንኡስ አንቀጽ 3 ላይ በተገለጸው መሰረት የሀገር ውስጥ ተጫራቾች ለሚሳተፉበት ብሄራዊ ግልጽ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም እንደሚገባና መ/ቤቱ ለተሻለ ውድድር ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን ብቻ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሊፈቅድ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ ሲሆን በመ/ቤቱና በተጫራቹ የቀረበው ሠነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበትና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲረጋገጥ ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ያለበት መሆኑን መመሪያው ቢያዝም፣ ይህ ተፈጻሚ ሳይደረግና በአማርኛ ቋንቋ በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጀው በአጠቃላይ የውል ድንጋጌ ላይ በጨረታው ሰነዱ የውል ስምምነት አ.ው.ሁ አንቀጽ 25.1 ላይ ውል ተቀባይ ውል የተገባላቸውን የእርማታ ብረቶች ለማስረከብ በሙሉ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ዕቃ ግምጃ ቤት ድረስ አጓጉዞ ቆጥሮ በራሱ ወጪ ያስረክባል፡፡ እንደዚሁ ርክክብ እስከሚፈጸም ድረስ የእርማታ ብረቶች ለማስረከብ የማጓጓዝ ኃላፊነት የውል ተቀባይ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የእርማታ ብረቶች ግዥ ተከናውኖ ሲጓጓዝ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በአቅራቢው በኩል የተዘጋጀው የውለታ ሰነድ በዩኒቨርሲቲው በኩል ያለአግባብ በመፈረሙ ምክንያት የትራንስፖርት ክፍያው በገዥው እንዲሸፈንና ተቋሙ መክፍል የማይገባውን ክፍያ በቀን 19/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 439206 ብር 883,610.70 ከጨረታው ሰነድ ውጭ ለጌታቸው ግርማ የጭነት የግል ትራንስፖርት ለእርማታ ብረት ማጓጓዣ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.21.2 <u>ስጋት፣</u>

ውለታው በመመሪያው መሰረት ካልተተገበሩ የመንግስትን ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም ሊውልና ለምዝበራና ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ የህግ ጥሰትንም ያስከትላል፡፡

2.21.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዕቃና አገልግሎት ግዢ ወቅት የሚደረጉ የግዢ አፈፃፀም መመሪያው የሚጠይቃቸው ሁኔታዎች አለማሟላት የመንግስት ጥቅም ሊያሳጡና ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲደረግ፡፡ በተጨማሪም ግዢዎች በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ብቻ መከናወን ስላለበት ለምን የህግ ጥሰት እንደተካሄደና በውሉ ስምምነት መሰረት እንዳልተፈጸመ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል። በመሆኑም ለወደፊቱ ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጽም፣ በውሉ ስምምነት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

2.21.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ከነትራንስፖርቱ እንዲቀርብለት የጠየቀ ቢሆንም የተወዳደሩት አቅራቢ ድርጅቶች በሙሉ የሞሉት ዋጋ ትራንስፖርትን እንደማያካትት በሰነዳቸው የገለጹ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የግንባታ ስራ የተቋረጠ ስለሆነ ጨረታው በድጋሚ ቢወጣ የሚወስደው ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የብረት ማጓጓዙን ስራ በራሱ በዩኒቨርሲቲው የተሰራ በመሆኑን፣

2.22.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከግዥ መመሪያ ውጭ የተፈጸመ ቅድሚያ ክፍያ፣</u>

በግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 አንቀጽ 16.26 በመንግስት የግዢ አፈጻጸም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል የሚሰጠውም ቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለጽ እንዳለበት ቢያዝም ዩኒቨርሲቲው፣

- በቀን 17/09/08 በባንክ ወጪ ማዘዣ ቁጥር 861561 ብር 17,447,400.00 ለአርማታ ብረት ግዥ ለኢስት ስቲል ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ የተከፈለ ሲሆን የሚሰጠውም ቅድሚያ ክፍያ መጠን ሳይገለጽ ሙሉውን /መቶ ፐርሰንት/ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በቀን 06/06/09 በባንክ ወጪ ማዘዣ ቁጥር 493354 ብር 2,390,022.00 ለሪየስ ኢንጅነሪንግ አክሲዮን ማህበር ለጀነሬተር ግዥ የተከፈለ ሲሆን

የሚሰጠውም ቅድሚያ ክፍያ መጠን ሳይገለጽ 95.94 በመቶ ቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በቀን 24/09/09 በባንክ ወጪ ማዘዣ ቁጥር 916923 ብር 566,432.50 የኤሌክትሪክ እቃዎች ግዥ ለኢዘዲን ሬድዋን ሁሴን ኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ የተከፈለ ሲሆን ንብረቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው ገቢ ከመሆኑ በፊት /መቶ ፐርሰንት/ ሙሉውን ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በድምሩ ብር 20,403,854.50 ሙሉውን ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.22.2 <u>ስጋት፣</u>

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም ይህም ቁጠባን ፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥትም ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም ሊውልና ለምዝበራም ሊጋለጥ ይችላል፡፡ የህግ ጥሰትንም ያስከትላል፡፡

2.22.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዕቃና አገልግሎት ግዢ ወቅት የሚደረጉ የግዢ አፈፃፀም መመሪያው የሚጠይቃቸው ሁኔታዎች አለማሟላት የመንግስት ጥቅም ሊያሳጡና ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲደረግ፡፡ በተጨማሪም ግዢዎች በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ብቻ መከናወን ስላለበት ለምን የህግ ጥሰት እንደተካሄደና በመመሪያው መሰረት እንዳልተፈጸመ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል።

2.22.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የእቃ ግዥ አቅርቦቶች 100% የሚከፈልበት ምክንያት አቅራቢዎች የእቃዉን ሙሉ ክፍያ ካልከፈለን ለማቅረብ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ዩኒቨርሰቲው ሌላ አማራጭ የሌለው በመሆኑና ከአቅም በላይ እየሆነ በመምጣቱ ያለው አማራጭ ክፍያውን በሙሉ መክፈል ወይም መተው ስለሆነና ክፍያው ሳይፈጸም ቢቀር ደግሞ ምን ችግር እንደሚፈጠር ሁኔታውን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናውን ተግባርሲሆን ለዚህ ዋነኛው

ምክንያት የፕሮፎርማ ግኘ በመሆኑ ወደፊት በተቻለ መጠን ማስቀረት የሚቻልበት መንገድ ካለ ለማስተካከል ሙከራ ይደረጋል።

2.23.1 <u>ግኝት፣ ለግንባታ ከውሉ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣</u>

ለኮንስትራክሽንና ለግንባታ ስራዎች የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ግንባታዎቹም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው እና ሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ መሃንዲሶች በገቡት ውል መሠረት ክፍያው ለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ አልታቤ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኦክሰዴሽን ፖንድ ለመገንባት በብር 29,665,483.68 ውል የገባ ሲሆን በገባው ውል መሰረት እስከ ታህሳስ 19/2009 ስራው እንደሚጠናቀቅ ቢያመለክትም እስከ ሚያዝያ 30/2009 ድረስ ብር 31,830,103.32 የተከፈለው ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ ውል ሳይኖረው ብር 2,164,619.64 ከውሉ በላይ በብልጫ የተከፈለው መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል።

2.23.2 <u>ስጋት፣</u>

ውለታ የተገባባቸውና ከፍተኛ የካፒታል በጀት ወጪ የተደረገባቸው ግንባታዎች በመመሪያው መሰረት ካልተተገበሩ የመንግስትን ገንዘብ ለምዝበራና ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

2.23.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከውሉ በላይ ለተፈጸመው ክፍያ ተጨማሪ የስራ ውለታ ወይም የለውጥ የሥራ ትእዛዝ /Supplementary & Variation Orders/ የተሟላ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፣ ካልሆነም ክፍያው አግባብ ስላልሆነ ገንዘቡ ተመላሽ ሊሆን ይገባል።

2.23.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

መጀመሪያ የኦክስደሽን ፖንዱ ዲዛይን ሲሰራ በዲዛይኑ ላይ በዙሪያው ላይ የውሀ መሸርሸርን የሚከላከል የድንጋይ ንጣፍ አልነበረውም:: ይህ የፍሳሽ ማጣሪያ ወይም ኦክስደሽን ፖንድ ግንባታ ስራ ሲሰራ አፈሩ በዝናብ ውሀ የሚታጠብና ጥቁር አፈር ወይም በተለምዶ ዋልካ የሚባል በመሆኑ የተሰራው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ አክስዴሽን

ፓንድ በደለል እንዳይሞላ ለማድረግ በዙሪያው ያለው ተዳፋት ቦታ በድንጋይ ርብራብ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ ይህም የግንባታ ስራውን ከተቀመጠው የውለታ የስራ ስፍር መጠን በላይ 7.3 ፐርሰንት እንዲጨመር አድርጎታል፡፡ ሆኖም ግን ሌላ አድስ ወይም ተጨማሪ ውል በአድስ ዋጋ ስራውን ከማሰራትና እንዲጠናቀቅ ከማድረግ ይልቅ ተጨማሪ የመጠባበቂያ በጀት የውለታው 10 ፐርሰንት (10% contingency) እስከሚሆን ድረስ ስራው ታምኖበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

2.24.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ የግንባታ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16 ንዑስ ቀጥር 25 መሠረት ከመንግሥት መ/ቤቱ ጋር ውል የገባው አቅራቢ በውሉ መሠረት አገልግሎቱን በወቅቱ ባለማቅረቡ በውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1ሺኛ የጉዳት ካሳ መክፈል እንደሚገባው እና የጉዳት ካሳው ከውሉ ዋጋ 10 በመቶ መብለጥ እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች በመመሪያው መሠረት ክትትል የሚደረግባቸውና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ በተለያዩ ተቋራጮች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ከግንባታ ጽ/ቤቱ በተገኘ መረጃና ትንተና እንዲሁም በመስክ በኦዲት ቅኝት ሲደረግ፣

- አልታቤ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዋናው የመግቢያ በር ግንባታ በብር 4,417,537.11 እስከ ህዳር 25/2007 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 85.46% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ946 ቀናት ወይም ከ2 ዓመት ከ7 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሚጅ/ 4,417,537.11 *946*1/1000=4,178,990.11 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 4,417,537.11 * 10%= 441,753.71 ገቢ አለመደረጉን፣

- ጠዳት ስራ ተቋራጭ የመምህራን መኖሪያ ህንጻ AP2/2; AP2/3 እና 1/1 ግንባታ በብር 50,393,414.6 በተገባ ውል እስከ 04/13/2008 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 66% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ116 ቀናት ወይም ከ3 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 50,393,414.6 *116*1/1000=5,845,636.09 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 50,393,414.6 *10% = ብር 5,039,341.46 ገቢ አለመደረጉን፣
- ሽመልስ ዓንጉል ስራ ተቋራጭ የመምህራን ቢሮ ህንጻ T-1 እና TM-2 ግንባታ በብር 27,647,417.88 በተገባ ውል እስከ 04/13/2008 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 74% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ301 ቀናት ወይም ከ10 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሚያዝያ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 27,647,417.88 *301*1/1000=8,321,872.78 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 27,647,417.88 *10% = ብር 2,764,741.79 ገቢ አለመደረጉን፣
- ሽመልስ ዓንጉል ስራ ተቋራጭ የእንሰሳት ማደለቢያ ግንባታ በብር 9,243,081.54 በተገባ ውል እስከ ህዳር/10/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 79.54% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ230 ቀናት ወይም ከ7 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 9,243,081.54 *230*1/1000=2,125,908.75 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ

10% መብለጥ ስለሌበት 9,243,081.54 *10% = ብር 924,308.15 ገቢ አለመደረጉን፣

- ዳንኤል ፀጋዬ ስራ ተቋራጭ የመንገድ ስራ ግንባታ በብር 16,018,830.02 በተገባ ውል እስከ ታህሳስ 30/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 88.96% ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ180 ቀን ወይም ከ6 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሚያዝያ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 16,018,830.02 *180*1/1000=2,883,389.40 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 16,018,830.02 * 10% = 1,601,883.00 ገቢ አለመደረጉን፣
- ዳንኤል ፀጋዬ ስራ ተቋራጭ የመኪና ማቆሚያ ግንባታ በብር 8,936,354.83 በተገባ ውል እስከ መስከረም 03/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 46.63% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ297 ቀናት ወይም ከ ከ9 ወር በላይ የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 8,936,354.83 *297*1/1000=2,654,097.38 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 8,936,354.83 *10% = ብር 893,635.48 ገቢ አለመደረጉን፣
- ዳንኤል ፀጋዬ ስራ ተቋራጭ የእግረኛ መንገድ ግንባታ በብር 19,967225.28 በተገባ ውል እስከ መጋቢት 05/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 62.15% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ115 ቀናት ወይም ከ3 ወር በላይ የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 19,967225.28 *115*1/1000=2,296,230.90 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 19,967,225.28 *10% = ብር 1,996,722.52 ገቢ አለመደረጉን

- ዳንኤል ፀጋዬ ስራ ተቋራጭ አስፋልት ስራ ቁጥር 2 ግንባታ በብር 13,549,696.80 በተገባ ውል እስከ ሚያዝያ 03/2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታዎቹ ደረጃ (Project status) 45.67% ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ87 ቀናት ወይም ከ2 ወር በላይ የዘገየ ሲሆን የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ እስከ ሰኔ 30/09 ድረስ የጉዳት ካሣ /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 13,549,696.80 *87*1/1000=1,178,823.62 ገቢ አለመደረጉን፤

በድምሩ ብር 17,724,599.13 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.24.2 ስጋት፤

- የወጣው የመንግስት የግዥ መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡
- ግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቅ በተቋሙ የመማር ማስተማር (በተማሪዎች ቅበላ፣ በተግባር ትምህርት አሠጣጥ) በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.24.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ ግንባታዎች ተጠናቀው ለተፈለጉበት ዓላማና አገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተቋራጮች በውል መሰረት ግንባታዎቹን አጠናቀው እንዲያስረክቡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳውም በውሉ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2.24.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፤

- አልታቤ ኃ/የተ/የግል ማህበር በብር 4,417,537.11 የዩኒቨርሲቲውን ዋና በር ሰርቶ ለማስረከብ ውለታ የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለተሰሩ ስራዎች ብር 982,999.73 ክፍያ ለደርጅቱ ተፈጽሟል። ይህም ከውለታው አንጻር ሲታይ 22.25% ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በጀት ዓመት የግንባታው ደረጃ (project status) 85.46% ላይ የሚገኝ ሲሆን ቀሪው ብር 3,434,537.38 የዋጋ ንረት ማካካሻ ክፍያን ሳይጨምር ተቋራጩ ክፍያ ሳያቀርብ ስራውን እየሰራ በመቆየቱ

የፕሮጀክቱን መልካም ፍጻሜ በመሻት ተቋራጩ ያልተከፈለው ገንዘብ ለጉዳት ካሳ ሊውል እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ እስካሁን ቆይተናል፡፡ ተቋራጩ የሰራበትን ክፍያ እንዳቀረበ የጉዳት ካሳውን በማሰብ ወደ ዩኒቨርሲቲው ተቀናሽ ተደርጎ ገቢ የሚደረግ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

- የግንባታ ስራው የዘገየበት በተረጋገጠ ተጨባጭ ማስረጃና ምክያት መሆኑ ወይም አለመሆኑ ቀርቦ ሲረጋገጥና ሲጸድቅ በውሉ መሰረት ተቋራጩ ሊቀጣ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ተቋራጩ በየጊዜው ተከታትሎ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ በማቅረብ ማጸደቅ ያለበት ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2009 አንድ ጊዜ ብቻ ለአማካሪ መሀንዲሱ በማቅረብ የአማካሪ መሀንዲሱ አስተያየት ተጨምሮበት በዩኒቨርሲቲው በኩል ቀርቦ የጸደቀው 123 ካሌንደር ቀናት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ስራን ሊያዘገዩ የቻሉ ጉዳዮች (በዩኒቨርሲቲው በኩል መቅረብ የነበረባቸው የአርማታ ብረትና የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት፣ እንዲሁም የአልሙኒየም ፕሮፋይል አቅርቦት ችግር፣ በክረምት ዝናብ የተፈጠረ የስራ መስተጓጎል ወዘተ) ቀርበው በመታየት ላይ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በመረጃ ላይ ተደግፎ ላልቀረበ የባከነ ጊዜና ላልቀረበ አገልግሎት (undelivered service) ቅጣቱን ተግባራዊ እናደርጋል፡፡
- ሽመልስ ጓንጉል ህንጻ ስራ ተቋራጭ የእንስሳት ማደለቢያ ቤት ግንባታ ለማከናወን ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውለታ የገባ መሆኑ ይታዎቃል፡፡ ሆኖም ለግንባታው መዘግየት ዋነኛው ምክንያት ዩኒቨርሲቲው እንዲቆም ያዘዘ በመሆኑ ነው፡፡
- ዳንኤል ፀጋየ ህ/ስ/ተ የመንገድ ስራ ግንባታ በብር 16,018,830.02 ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውለታ የገባ ሲሆን መጠናቀቅ ከነበረበት የውለታ ጊዜ 6 ወር የዘገየው በዋናነት የመንገድ ስራ በክረምት ወቅት ሙሉ ለሙሉ መስራት ስለማይችል እንዲቆም በመደረጉና የሚሰራው መንገድ እየተገነቡ ከሚገኙ የመምህራን መኖሪያ አፓርትመንቶች፣ቢሮዎችና መማሪያ ህንጻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የህንጻዎቹን መጠናቀቅ ስለሚጠብቅና በሌሎቹ ላይ መንገዱ ለሚገነቡት ህንዎች መንቀሳቀሻ ሆኖ ስለሚያገለግል የመንገዱ የመጨረሻ ስራ እንዲጠናቀቅ ባለመደረጉ የተፈጠረ ሲሆን ለዚህም ከባለቤት ወይም ከአማካሪ መሀንሱ የስራ ትዕዛዝ ውጭ በሆኑ ምክኒያቶች

የባከኑ ጊዜያትን ለማወቅ በወቅቱ ለአማካሪ ድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ የጊዜ ማራዘሚያ አቅርበው ባለመጽደቁ የተፈጠረ ችግር መሆኑን እንገልጻለን፡፡

- ዳንኤል ፀጋየ ህ/ስ/ተ የመኪና ማቆሚያ ግንባታ በብር 8,936,354.83 ለመስራት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውለታ ፈጽመዋል፡፡ ይህ ስራ በውለታ ጊዜው እንዲጠናቀቅ ቢፈለግም በውለታ ላይ የተቀመጠው ዲያሜትር 127ሚ.ሜ ብረት ገበያ ላይ ባለመገኘቱ በወቅቱ ገበያ ላይ በተገኘው በባለ200ሚሜ ዲያሜትር ብረት እንዲቀየር የድዛይን ለውጥ በመደረጉ ነው፡፡
- ዳንኤል ፀጋየ ህ/ስ/ተ የእግረኛ መንገድ ግንባታ በብር 19,967,225.28 ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውለታ የፈጸሙ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መጠናቀቅ ከነበረበት የውለታ ጊዜ 3 ወር የዘገየው በዋናነት የመንገድ ስራ በክረምት ወቅት ሙሉ ለሙሉ መስራት ስለማይችል እንዲቆም በመደረጉና የሚሰራው መንገድ እየተገነቡ ከሚገኙ ህንጻዎች ጋር የተያያዘ በመሆኑ የህንጻዎቹን መጠናቀቅ ስለሚጠብቅና በሌሎቹ ላይ መንገዱ ለሚገነቡት ህንዎች መንቀሳቀሻ ሆኖ ስለሚያገለግል የመንገዱ የመጨረሻ ስራ እንዲጠናቀቅ ባለመደረጉ የተፈጠረ ሲሆን ለዚህም ከባለቤት ወይም ከአማካሪ መሀንሱ የስራ ትዕዛዝ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች የባከኑ ጊዜያትን ለማወቅ በወቅቱ ለአማካሪ ድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ የጊዜ ማራዘሚያ አቅርበው ባለመጽደቁ የተፈጠረ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
- ዳንኤል ፀጋየ ህ/ስ/ተ የአስፋልት ስራ ቁጥር ሁለት ግንባታ በብር 13,549,696.8 ለመስራት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውለታ መግባቱ ይታወቃል፡፡ ስራው እንዲሰራ ለዳንኤል ጸጋዬ ህ/ስ/ተቋራጭ ሲሰጥ በመጀመሪያ አልታቤ ኃ/የተ/የግል ማህበር የመንገድ ቆረጣና ሙሊት ስራውን እንዲሰራ ተሰጥቶት የማስተካከያ ስራ ባለማጠናቀቁና ባለማስረከቡ የአስፋልት ስራ ውለታ ወስዶ የሚሰራው ዳንኤል ጸጋዬ ህ/ስ/ተቋራጭ መንገዱን ተረክቦ መስራት ባለመቻሉ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአስፋልት መንገዱን ለመስራት በክረምት ወራት የባከኑ ቀናት በመኖራቸው ነው፡፡

3. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

3.1 ግኝት፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5/መ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት በወቅቱ መወራረዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰኔ 30/2009 በሪፖርቱ ከሚታየው ብር 138,374,327.75 ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 4201 ልዩልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች /suspense/ የተሰጠ ብር 114,172.16 ከዚህ ውስጥ ብር 33,423.13 ከአንድ ዓመት እስከ አራት ዓመት በተሰብሳቢ ተይዞ መቆየቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4204 ለማህበራዊ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ቅድሚያ ክፍያ/Advance for SSDP/ ለአባይ ኢንዱስትሪያል አክሲዮን ማህበር ከውስጥ ገቢ ለቦንድ ግዥ የተከፈለ ብር 3,075,000.00 ከአንድ ዓመት በላይ በተሰብሳቢ ተይዞ መቆየቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4210 በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች / Other Advance Within Government/የተሰጠ ብር 12,624,831.34 ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 10,613,056.8 ከ1 ዓመት እስከ አምስት ዓመት በተሰብሳቢ ተይዞ መቆየቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4251 ለስራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ / Advance to Contractors / ከተሰጠ ብር 99,868,075.14 ውስጥ ብር 3,576,879.78

ኮንትራክተሮቹ ስራውን ያቋረጡና ከስድስት ዓመት በላይ በተሰብሳቢ ተይዞ መቆየቱን፤

- በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቅራቢዎች የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ/ Advance to supplier/ ብር 22,279,841.57 ዕቃው ገቢ ባለመደረጉ ከአራት ወር እስከ አራት ዓመት በላይ ሂሳቡ ሳይወራረድ መገኘቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4254 ከመንግስት መ/ቤቶች ውጭ ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች/Other advance outside government/ ለጀምበር ሁለገብ የገበሬዎች ህ/ሥ/ማህበር የተሰጠ ብር 7,569.08 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ መገኘቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4272 ለህብረት ስራ ማህበራት /Cooperatives/ ለእንጀራ አቅራቢ ጸሃይ አዲሴ እና ጓደኞቹ የተሰጠ ብር 106,799.16 ከሁለት ዓመት በላይ ሳይወራረድ መገኘቱን፤
- በሂሳብ መደብ 4273 ለግለሰቦችና የግል ድርጅቶች /Individuals and private organization/ የተሰጠ ብር 17,936.00 ከሶስት ዓመት በላይ ሳይወራረድ መገኘቱን፤

በድምሩ ብር 39,710,505.52 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ እና በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

3.2 ስጋት፤

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ሊወራረድ የሚችለውን እንዲወራረድ፣ ሊወራረድ የማይችለውን ደግሞ ደንቡ በሚያዘው መሠረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተቋሙ ተመሳሳይ

ሁኔታ እንዳይከሰት በቅድሚያ ወጪ በሚደረጉ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በተሰጠው አስተያየት መሰረት ክትትል እየተደረገ የሚሰራ መሆኑን እንገልጻለን
- ለአባይ አክሲዮን የተከፈለው ክፍያ በአሁኑ ወቅት የወጪ እውቅና እንዲሰጠው ተደርጓል
- ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት፣ ለጅንአድ፣ ለመንገስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ደብዳቤ ቢጻፍም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም። ችግሩን መፍታት ካልተቻለ ጉዳዩን ወድፍርድቤት ለመውሰድ በምክክር ላይ ነን።
- ለህንጻ ስራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ስራውን ያቋረጡ በመሆኑና ግንባታዎቹ የመጨረሻ ርክክብ ባለመደረጉ የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ መሰብሰብ ባለመቻሉ ነው፡፡
- ጉዳዩ ወደ ህግ ክፍል ተላልፎ በህግ ክፍል አማካኝነት ገንዘቡ ብር 7569.09 ወደ መንግስት ሳጥን ተመላሽ ተደርጓል።
- ጉዳዩ ወደ ህግ ክፍል ተላልፎ በህግ ክፍል አማካኝነት ገንዘቡ ወደ መንግስት ሳጥን ተመላሽ ተደርጓል፣
- ክትትል እየተደረገበት ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚመለስ ይሆናል።

4. <u>በጀት፣</u>

4.1 <u>ግኝት፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2009 በጀት ዓመት የተመደበው የወጪ በጀትና ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ከመደበኛና ካፒታል በጀት ብር 59,644,766.67 ሥራ ላይ ያልዋለ እና ብር -48,993,357.87 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት እስከሰኔ 30/2009	ሥራ ላይ የዋለ በጀት እስከ ሰኔ 30/2009	ያልተሰራበት በጀት እስከ ሰኔ 30/2009	ያልተሰራበት መደበኛ በጀት በመቶኛ (%)
6213	1,745,682.00	1,388,024.57	357,657.43	20.49
6215	3,300,000.00	2,706,774.22	593,225.78	17.98
6217	5,962,333.00	4,731,800.21	1,230,532.79	20.64
6219	379,800.40	296,401.14	83,399.26	21.96
6223	465,000.00	415,049.89	49,950.11	10.74
6243	676,000.00	605,115.88	70,884.12	10.49
6244	1,500,000.00	1,031,502.90	468,497.10	31.23
6252	2,339,930.00	1,685,550.54	654,379.46	27.97
6253	440,000.00	349,586.23	90,413.77	20.55
6254	650,000.00	543,552.65	106,447.35	16.38
6256	7,419,970.69	6,106,190.11	1,313,780.58	17.71
6257	1,400,000.00	926,829.04	473,170.96	33.80
6259	330,060.00	248,416.49	81,643.51	24.74
6313	61,491,514.43	53,087,659.90	8,403,854.53	13.67
6322	147,339,270.00	131,663,789.01	15,675,480.99	10.64
6323	103,061,412.00	73,150,264.09	29,911,147.91	29.02
6417	548,800.00	468,498.98	80,301.02	14.63
ድምር	**339,049,772.52**	**279,405,005.85**	**59,644,766.67**	
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት እስከ ሰኔ 30/2009**	**እስከ ሰኔ 30/2009 ወጪ**	**ከበጀት በላይ የወጣ እስከ ሰኔ30/2009**	**ከበጀት በላይ የወጣ በ% በመቶኛ**
6116	7,143,840.80	8,606,151.33	-1,462,310.53	-20.47
6221	960,110.00	1,112,442.12	-152,332.12	-15.87
6314	15,983,747.00	31,327,400.51	-	-96.00
6315	60,000.00	445,850.00	-385,850.00	-643.08
6324	68,037,904.00	97,187,115.71	-	-42.84
6412	1,100,000.00	3,600,000.00	-2,500,000.00	-227.27
ድምር	**93,285,601.80**	**142,278,959.67**	**-**	

4.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቀቀምና አያያዝ ስርዓቱ በአግባቡ ካልተጠቀመ ዓመታዊ ዕቅዱን ሊያዛባ ከመቻሉም በላይ በሌሎች መ/ቤት /ተቋማት/ ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ይሆናል። ከበጀት በላይ መጠቀምም የህግ ጥሰትን ሊያስከትል ይችላል።

4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡
- ከተፈቀደለት በጀት በላይ መጠቀም አግባብነት የሌለው ስለሆነ የበጀት አጠቃቀም እና አወጣጥ ስርዓት ማኔጅመንቱ ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከበጀት በላይ ጥቅም ላይ ውለው የታዩት በጀቶች የመንግስትን መመሪያ እና ደንብ ጥሰትን የሚያሳዩ ስለሆነ አስፈላጊው የበጀት ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በኦዲት የተሰጠው አስተያየት ስጋት እና የማሻሻያ ሃሳቦች ተቀባይነት ያላቸው በመሆናቸው ማነጅሜንቱ ለቀጣዩ ትኩረት ከሚያደርግባቸው አንካር ጉዳዩች እንዱ ስለሆነ አስተካክለን እንቀጥላለን፡፡
- በኦዲት የተሰጠው የስጋት አስተያየት ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በ2009 በጀት አመት የክፍያ ሰርተፊኬት ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የቀረበው የሰኔ ወር ካፒታል በጀት ጥያቄ እስከ ብር 46 ሚሊዮን ክፍያ በችሮታ ጊዜ ይከፈላል ተብሎ ሳይለቀቅ ቀርቶ በችሮታ ጊዜም የተጠየቀው ገንዘብ ባለመለቀቁ የቀረ በጀት ነው፡፡

5. <u>ንብረት፣</u>

5.1.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 1 መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል። በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲውን የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ በተደረገው ኦዲት፡-

1. <u>የቋሚ እቃዎች እስቶርን በሚመለከት፣</u>
   - አዲስ ቋሚ እቃዎች ከአሮጌ ተመላሽ እቃዎች ጋር በአንድ ስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡
   - የተበላሹ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ፣5 ፕሮጀክተሮች ፣ 31 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች ፣3 ፕሪንተሮች ፣ 1 ሶኒ ቴሌቪዥን ባለ 42 ኢንች ፣ 5 ቲፕ ሊንክ ዋየርለሶች ፣ 1 ሲስኮ ካታሊስት ፣ ብዛት ያላቸው የማይሰሩ ዩፒኤሶች እና ቻርጀሮች ፣ 13 አሮጌ ተመላሽ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ፣ በብልሽት ምክንያት የማይሰሩ 12 የዋይፋይ ኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥባቸው መሳሪያዎች ፣ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆኑ፡፡
   - በባለ 25 ሊትር ጀሪካን የተቀመጠ አሲድ በቀላሉ ሊቀጣጠሉ ከሚችሉ ጎማዎች እና ሌሎች እቃዎች ጋር አደጋ ሊፈጥር በሚችል መልኩ በእስቶሩ ውስጥ የተቀመጠ መሆኑ፡፡
   - አሮጌ ፍራሾች እና ትራሶች ፣ብዛት ያላቸው አሮጌ /ተመላሽ/ ወንበሮች፣ ብዛት ያላቸው አሮጌ ጎማዎች ሳይወገዱ በእስቶሩ ውስጥ ያሉ መሆኑ፡፡
   - 2 አዲስ ቫዮሊን የሙዚቃ መሳሪያዎች እና 6 አዳዲስ ባለመደገፊያ ወንበሮች ያለአገልገሎት ከአሮጌ /ተመላሽ /እቃዎች ጋር ተደባልቀው መቀመጣቸው፡፡
   - በ2009 ዓ.ም በውድ ዋጋ ተገዝተው ገቢ የተደረጉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ግዥው እንዲገዛለት ለጠየቀው ክፍል ሳይሰጡ በአባራም ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡ በ2007 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 57 External DVD Writer፣ 5 እስካነሮች ፣ 8 ፕሮጀክተር ስክሪንኖች 18

Lenevo ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ፣ 3 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ 5 ሲሊንደር ስቶቮች 1 ኦሎምፒያ ካልኩለተር ያለአገልግሎት የተቀመጡ፡፡

- 1 የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ 3 የሽንኩርት መፍጫ ማሽኖች፣ 2 የምግብ ማብሰያ ፕላንተሪ ሚክሰር፣ 2 ዊስከስ የምግብ ማብሰያ ማሽን፣ 10 News Paper storage ፣2 Subdistribution bord፣ 1 Endor Men Distribution Bord፣ 20 ዘመናዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፣

2. <u>የአላቂ እቃዎች እስቶርን በተመለከት፣</u>

- ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠ ግራፍ ቻርት ብዛት 437 ፤ ከ 9 ወር በላይ በብልሽት ምክንያት ያለ አገልግሎት የተቀመጠ ባለ 1000 ዋት ጀኔሬተር ፣ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጡ HRC የጀኔሬተር ፊዩዞች እና ፊልትሮዎች ከአላቂ እቃዎች ጋር በስቶሩ ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

- ዩኒቨርስቲው ሲቋቋም ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ ለምግብ ማብሰያ የሚሆኑ 5 ቦይለሮች ፣ 4 ባለ አራት ምድጃ ፣ 1 ባለ አንድ ምድጃ ፣ 15 የምግብ ማብሰያ እቃዎችና የመመገቢያ ሳህኖች የሚታጠቡባቸው መሳሪያዎች ፣ 5 ዘመናዊ የስፖርት መስሪያ አልጋዎች ፣ ብዛት ያላቸው አዳዲስ የብረት ፋይል ካቢኔቶች ያለ አገልግሎት በእስቶሩ ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

3. <u>የኮንስትራክስሽን እስቶርን በተመለከተ፣</u>

- እቃዎች ሲገቡና ሲወጡ እየተመዘገቡ የሚመዛዘኑበት ቢን ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ ፤ ስቶክ ካርድ የማመዛዘን ስራ የሚሰራ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ የሚሰራው በንብረት ግምጃ ቤት ባለሙያው መሆኑ፡፡
- እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው ተመላሽ /Westage / ፌሮዎች ፣ የጣሪያ ቆርቆሮዎች እና የቆርቆሮ በሮች ያለመፍትሄ በእስቶሩ አካባቢ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፡፡

4. <u>የግንባታ ጥገና እና እድሳት እስቶርን በተመለከተ፣</u>

- ንብረቶች ወደ እስቶሩ ሲገቡና ሲወጡ ስቶክ ካርድ የማመዛዘን ስራ የሚሰራ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ የሚሰራው በንብረት ግምጃ ቤት ባለሙያው መሆኑ፡፡
- የኤሌክትሪክ ፣ የቧንቧ እና ሌሎች የጥገና እና እድሳት መለዋወጫ እቃዎች ለብልሽት በሚዳርግ አቀማመጥ ተደበላልቀው የተቀመጡ መሆኑ፡፡

5. <u>የመኪና መለዋዎጫ እቃዎች እስቶርን በተመለከተ፣</u>

- እቃዎችን ለመለየት በሚያስቸግር አቀማመጥ ተደራርበው የተቀመጡ መሆናቸው እና እቃዎቹ ባሉበት አካባቢ ቢንካርድ ያልተቀመጠ መሆኑ፡፡
- የዩኒቨርስቲው መኪኖች ሲበላሹ የሚጠገኑት በአስመጪው ድርጅት እና በግል ጋራዦች በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ከገዛቸው የመለዋወጫ እቃዎች ውስጥ ሾክ አብሶርበሮች እና ኤየር ክሊነሮች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ከ 4 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

6. <u>የተማሪዎች ክሊኒክን በተመለከተ፣</u>

- በክሊኒኩ ዋና ስቶር ውስጥ ቢን ካርድ የሚጠቀሙ ሲሆን ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ የማመዛዘን ስራ የሚሰራ የንብረት ቁጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ ስቶክ የማመዛዘን ስራ ያልተሰራ መሆኑ ፡፡
- በመድሃኒት ማሰራጫ /በዲስፔንሰሪ / ክፍል ውስጥ ቢንካርድ የሚጠቀሙ ሲሆን ነገርግን መድሀኒቶች ገቢና ወጪ በሚሆኑበት ጊዜ ቢን ካርድ ወቅቱን ጠብቆ ያልተመዛዘነ /አብዴት/ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- መድሀኒቶች ከዋናው ስቶር ክፍል ወደ ዲስፔንሰሪ ክፍል ገብተው ተሰራጭተው ካለቁ በኋላ በድጋሚ ከዋናው ስቶር እንዲወጡ ከመደረጋቸው በፊት መድሀኒቶቹ በትክክል ለታካሚ ተማሪዎች ተሰጥተው ስለማለቃቸው በፕሪስክሪፕሽን ወረቀቶች ትዕዛዝ ወጪ የሆኑት መድሀኒቶች ከዋናው ስቶር ወደ ሚኒስቶር ገቢ ከሆኑት መድሀኒቶች ጋር የሚመዛዘኑበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፡፡

7. <u>አገልግሎት የማይሰጡ አሮጌ /ተመላሽ/ ቋሚ እቃዎችና አላቂ እቃዎች የተቀመጡበት እስቶርን በተመለከተ፣</u>

- እጅግ ብዛት ያላቸው አሮጌ /ተመላሽ/ የፕሪንተር እና የፎቶ ኮፒ ማሽን ቀለሞች /ካርትሬጆች/ ሳይወገዱ ከ 1 ዓመት በላይ ተከማችተው ያሉ መሆናቸው፡፡
- ሼልፎችና የእቃ ማመላለሻ ጋሪዎች ፣ ብዛት ያላቸው የተሰባበሩ ወንበሮች ፣ ብዛት ያላቸው ጠረጴዛዎች ፣እጅግ ብዛት ያላቸው አሮጌ ቁምሳጥኖች ፣ የእንጨት በሮች እና የቆርቆሮ በሮች ፣ ሎከሮች ሳይወገዱ ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

8. <u>የተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃዎች አያያዝና የማብሰያ እቃዎችን በሚመለከት፣</u>

- የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ለተግባር ትምህርት መስክ በሚሄዱበት ጊዜ አካዳሚክ ትምህርት ክፍሉ ለመስክ የሚሄዱ ተማሪዎችን ቁጥር ፣ ከመቼ ጀምሮ እንደሚሄዱ እና የመስክ የቆይታ ጊዜያቸውን እና የመመለሻ ጊዜያቸውን ጭምር ለተማሪዎች ምግብ ቤት ስለማያሳውቅ ምግብ ከተሰራ በኋላ በመትረፍ እየተበላሸ መሆኑ ይህም ዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ለተግባር ልምድ መስክ ሲወጡ በቀን ከሚከፍላቸው የምግብ ወጪ በተጨማሪ ያላግባብ ምግብ እየተሰራ በመሆኑ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እና ለኪሳራ እየዳረገው መሆኑ፡፡
- ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተጠራቀሙ የውሃ ባልዲዎች ፣ የውሃ ጆጎች ፣ የሻይ ኩባያዎች ፣ የፓስታ ማጥለያዎች ፣ የምግብ ማብሰያ ብረት ድስቶች እና የፕላስቲክ የውሃ በርሜሎች ሳይወገዱ በምግብ ቤት አካባቢ ባሉ እስቶሮች ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡
- 3 የሸንኩርት መፍጫ ማሽኖች ፣ 1 የሊጥ ማቡኪያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆናቸው ፡፡ እንዲሁም ብዛት ያላቸው አሮጌ የዳቦ ማስቀመጫ ቅርጫቶች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፡፡

- በ2008 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 2 የስጋ መፍጫ ማሽኖች አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

5.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ተገቢው የንብረት አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- እንዲሁም ንብረቶች በአግባቡ ባለመጠበቃቸው ለተጨማሪ ብልሽትና ወጪ ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

5.1.3 <u>ማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ በኩል በታዩት ድክመቶች ላይ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በአግባቡ ባለመቀመጣቸው ለብልሽት በመዳረግ ላይ የሚገኙት ንብረቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች ላይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

5.1 <u>**ቋሚ እቃ**</u>

- መጋዘኑ አንድ ይሁን እንጂ ሲሰራ ጀምሮ ተከፋፍሎ የተሰራ በመሆኑ ንብረቶቹ የተቀመጡት የካይዘን አሰራር ፍልስፍናን መሰረት በማድረግ ተደራጅተው የተቀመጡ ናቸው።
- የተሰጠው አስተያየት ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በንብረቶቹ ላይ ማኔጅሜንት ካውንስሉ በወሰነው መሰረት በሰቶር ላይ የነበሩት ላፕቶፖች ተጠግነው አገልገሎት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ሌሎቹ ግን በባለሙያ ታይተው ተጠግነው ስራ ላይ የሚውሉ መሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ የመለዋወጫ ግዥ ታዞ በመጠባበቅ ላይ መሆኑን እንገልጻለን
- አሲዱ እንዲቀመጥበት የተሰጠው አስተያየት መሰረት በማድረግ ተግባራዊ እናደርጋለን።

- በንብረት ግምጃ ቤት የነበሩ ያልተወገዱ ተብለው አስተያየት የተሰጠባቸው 26 ፍራሾች በአሁን ወቅት ለተቋሞች ተስጥተዋል። ሌሎቹ ቁሳቁሶች በስቶር ላይ የተገኙት በዩኒቨርሲቲው ለሚቋቋመው ወርክሾፕ ግብአት ይሆናሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው።
- የንብረት አሰተዳደር ዳይሬክቶሬት መጋዘኖቹን እያደራጀ ባለበት ወቅት ኦዲተሮቹ በመምጣታቸው ምክንያት የታየ እንጂ ቀደም ብሎ ይሁን በአሁን ወቅት ተደበላልቆ የሚገኝ ንብረት የሌለና ሁሉም በስርአት የተደራጀ መሆኑን እናሳውቃለን።
- በንብረት ክፍል የተገኙ ያልተከፋፈሉ ቋሚ ንብረቶች የሙዚቃ መሳሪያ፣ External hard disc፣ የፕሮጀክተር ስክሪን፣ የስቶቭ ሲልነደር በቀጣዩ የሚሰራጩ ሲሆን ሌሎቹ ግን ወጭ የተደረጉ መሆኑን እናሳውቃለን።
- ለተማሪዎች የምግብ ማብሰያና ማዘጋጃ ተብለው በመጠባበቂያነት የተገዙ ናቸው። ምክንያቱም መጠባበቂያ ከሌለ በአገልግሎት ላይ ያሉ ማሽኖች ቢበላሹ ለማስጠገን ሆነ በሌላ ለመተካት የሚወስደው ሂደት ረዥም በመሆኑ ይህንን ታሳቢ መሰረት በማድረግ ተገዝተው በመጠባበቂያነት የተቀመጡ መሆኑ ይታወቅልን።

5.2 <u>አላቂ እቃ</u>

- በግኝት አሰተያየት የተቀመጠው የተቀበልነው ሲሆን በአሁን ወቅት ሁሉንም አስተካክለናል።
- በቀደም ሲል በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተገዝተው የመጡ የምግብ ማብሰያ ግብአቶች ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌትሪክ ፍጆታ ስለሚጠቀሙና በቀላሉም ስለማይግሉ በአሁን ወቀት እነዚህን የምግብ ማብሰያ እቃዎች ለመጠቀም ካለው የኤሌትሪክ መቆራረጥና ሃይል ማነስ አስቸጋሪ በመሆኑ ከምግብ ቤት ወጥተው በመጋዘን የተቀመጡ መሆናቸውና ፋይል ካቢኔቶቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው ስለሆነ በቀጣይ ስርአት ባለው መንገድ

የሚወገዱት የሚወገዱ፣ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

5.3 **የኮንስትራክሽን እቃዎች ስቶር በተመከተ**

- በኮንስትራክን ስቶር የተሰጠውን አስተያየት በመዋቅር ክፍተት የተፈጠረ በመሆኑ ለወደፊቱ እንዲስተካከል እናደርጋለን
- በቁርጥራጭ ብረቶች ላይ የተሰጠውን አስተያየት ተገቢ ስለሆነ ተቀብለን እናስተካክላለን

5.4የግንባታና ጥገና ስቶር በተመለከተ

- ➢ በግንባታና እድሳት ስቶር የተሰጠውን አስተያየት በመዋቅር ክፍተት የተፈጠረ በመሆኑ ለወደፊቱ እንዲስተካከል እናደርጋለን
- ➢ በእቃዎቹ ሰፊ ቦታ የሚጠይቁ ቢሆንም ያለን መጋዘን ጠባብ በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት ሲሆን የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለን ተግራዊ እናደርጋለን

5.5የመኪና መለዋወጫ ስቶር በተመለከተ

- በሰቶር ቢን ካርድ የተሰጠው አስተያየት ዩኒቨርሲቲውን የማይገልጽ ስለሆነ አልተቀበልነውም
- የተሰጠው አስተያየት ተቀብለን እናሰተካክላለን

5.6የተማሪዎች ክሊኒክ በተመለከተ

- የመዋቅር ችግር ስለሆነ አስተያየቱን ተቀብለን ለወደፊቱ እናስተካክላለን
- አስተያየቱን ተቀብለን ለወደፊቱ እናስተካክላለን

5.7. **አገልግሎት የማይሰጡ ተመላሽ እቃዎች**

- በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ደብዳቤ ተጽፎ ካርትሬጆቹ ለናኖዳስ እንድናስረክብ የተገለፀልን ቢሆንም ካርቲሬጆቹ የሚረከብ አካል መጥቶ ካልተረከበ ዩኒቨርሲቲው ወደ ተረካቢ ድርጅት አጓጉዞ ለማስረከብ ለማስረከቢያ ከተወሰነለት ዋጋ በላይ ተጨማሪ ወጭ ስለሚያስከትል ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፣
- ለሚቋቋመዉ ወርክ ሾፕ ግብአት የሚውሉ በመሆኑ አልተወገዱም፣

- ለተማሪዎቸ ለተለያዩ የተግባር ትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ከትምህርት ክፍል መረጃ ለተማሪዎቸ ምግብ ቤት ስለሚደርስ የምግብ መባከን አይፈጠርም፤ ነገር ግን የሚደፋውን ምግብ ተማሪዎቹ ተመግበው የሚተርፋቸውና የሚመልሱት አሁን ባለው ሁኔታ ምንም ሊደረግ የሚችል ነገር የለም። ሆኖም ይህንንም ትራፊና ሌሎች ተረፈ ምግቦችን አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስችል መሳሪያ ለመግዛት የግዥ ትእዛዝ ተሰጥቷል።
- የሚወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ ለየክፍሎች ደብዳቤ ተጽፎ ምላሽ የሰጡትን የማስወገድ ስራ የተሰራ ሲሆን በምግብ ቤት የሚገኙ የሚወገዱ ንብረቶቸ ዘግይተው ሪፖርት የተደረጉ እና ተጠግነው ስራ ላይ የሚውሉና የማይውሉ እስኪለዩ ድረስ ለቀጣዩ የተቀመጡ ናቸው።
- ለተማሪዎች የምግብ ማብሰያና ማዘጋጃ ተብለው በመጠባበቂያነት የተገዙ ናቸው:: ምክንያቱም እስካሁን ባለን ልምድ መጠባበቂያ ከሌለ በአገልግሎት ላይ ያሉ ማሽኖች ሲበላሹ ለማስጠገንም ሆነ በሌላ ለመተካት የሚወስደው ሂደት ረዥም ስለሆነ ችግር እየገጠመን በመሆኑ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ተገዝተው የተቀመጡ ናቸው::

5.2.1 <u>ግኝት፣ በቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ ህንጻ፣</u>

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 65 የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኙ ንብረቶችን ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን ለእያንዳንዱ ንብረት የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ወይም በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ስርአት በመጠቀም መዝግቦ መያዝ እንዳለበትና የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውነው የስራ ክፍል የተጠናከረ መረጃ የያዘ የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለበት ያዛል። በተጨማሪም በፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር

መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 2 ቁጥር 7(2) (ሀ-ሐ) ዩኒቨርስቲው ያጠናቀቃቸው የግንባታ ስራዎች ቀጥተኛ ወጪዎችንና የአስተዳደርና ምክር አገልግሎትን ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን አስፈላጊውን መረጃ በማሟላት የተጠናቀቁ ግንባታዎች በዩኒቨርስቲው በቋሚ ንብረት ካርድ በሀብትነት መመዝገብ እንዳለባቸው ቢያዝም ያልተመዘገቡ መሆናቸው ለማወቅ ተችሏል፤፤

5.2.2 <u>ስጋት፤</u>

ተገቢው የንብረት አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ የመንግስት መመሪያን ተግባራዊ ከአለመሆኑም በላይ ለብላሹ አሰራር ያጋልጣል፡፡

5.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ዩኒቨርሲቲው ግልፅ ፤ዘመናዊ ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር በማስፈን በእጁ ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፤ የመቆጣጠርና አገልግሎቱ ሲያበቃ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዲያስችለው ሥራ አመራሩ ከላይ የተዘረዘሩትን ድክመቶች፣ የአሰራርና የአፈፃፀም ግድፈቶች በመመልከት ስለቋሚ ዕቃዎች የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ባማከለ መልኩ አፋጣኝ የማስተካከያ እና የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

5.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

- ሁሉም ቋሚ ንብረቶች በመዝገብ ተመዝግበው የተያዙ ሲሆን ህንጻዎቹ ግን ሙሉ ለሙሉ ርክክብ ያላለቀላቸው በመሆኑ በተሟላ ሁኔታ ታሪካቸው ተጠናቅሮ ለንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባለመላኩ ምክንያት የተፈጠረ ችግር መሆኑ ታውቆ ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ክትትል ተደርጎ እንደሚሰራ እናረጋግጣለን።

6. ልዩ ልዩ፤

6.1.1 ግኝት፤ የ2007 እና 2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አወሳሰድ፤

1. ከ2008 በጀት ዓመት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሀሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የ2007 እና 2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ጋር በገባው ውል መሠረት የግንባታ ሥራዎች በወቅቱ ባለመጠናቀቃቸው ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሣ በድምሩ ብር 53,759,140.43 መገኘቱን፤
- ዩኒቨርሲቲው ከኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ጋር ውል በመግባት በብር 4,614,348.22 የጀነሬተር ግዥ የፈፀመ ሲሆን፤ በውሉ መሰረት ዕቃው በወቅቱ ገቢ ባለመደረጉ ላዘገየበት 463 ቀናት መከፈል የሚገባው የጉዳት ካሣ ብር 461,434.82 ገቢ መሆኑ፤
- የዩኒቨርሲቲው የግንባታ መሐንዲስ በቦታቸው በመሐንዲስነት የሚያገኙት ደመወዝ ሊከፈላቸው ሲገባ፣ በቦርዱ ውሳኔ በምክትል ስራ አስኪያጅ ደረጃ እንዲሰሩ በመደረጉ ለቦታው የሚከፈለው ደመወዝ እንደ ማበረታቻ (Top up) በየወሩ እንዲከፈላቸው የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በቁጥር ወዩ/1352/01-

ፕ/06 ባሳወቀው መሰረት ከሰኔ/2006--ሰኔ30/2008 በድምሩ ብር 65,245.00 አለአግባብ ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱን፣

- የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል ሰኔ 2004 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 4 መሠረት መከፈል ሲገባው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ለመጡ እና ሲምፖዝየም ላይ ንግግር ላደረጉ መምህራን ከተፈቀደው የውሎ አበል የክፍያ ተመን በላይ ከብር 2,000.00 እስከ ብር 5,000.00 እንዲከፈላቸው በመደረጉ በድምሩ ብር 49,000.00 ከመደበኛ የውሎ አበል በተጨማሪ ያለ አግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣
- በትርፍ ሰዓት ለሚያስተምሩ መምህራን በየማዕረጋቸው በወጣው የክፍያ ተመን መሠረት በክሬዲት ሀወር (credit hours) ክፍያ እንደሚከፈል ከኢ.ፌ.ደ.ሪ ጠ.ሚ ጽ/ቤት ጥር 13/2003 ዓ.ም በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ቢገለፅም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በትርፍ ሰአት ለማስተማር ለመጡ መምህራን በአንድ የትምህርት ሰዓት (credit hour) እንዲከፈላቸው ከተፈቀደው የገንዘብ ተመን በላይ እንዲከፈላቸው በመደረጉ አለአግባብ ብር 43,082.00 ወጪ ሆኖ መገኘቱን፣
- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር መ30/ጠ13/368/3 በሰኔ 29/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው መመሪያ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ እንዲቆም በቁጥር መ30/ጠ13/37/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ለሰሩበት በሚል የትርፍ ሰዓት ክፍያ በድምሩ ብር 1,691,768.94 ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍያ ፈፅሞ መገኘቱን፣
- የክረምት ክፍያ እንዲፈጸም የዩኒቨርሲቲው ሰኔት ለአስተዳደር ቦርዱ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ቦርዱ ክፍያውን እንዲያፀድቀው እና በዩኒቨርሲቲው ሰኔት እንዲወሰን በማድረግ የትምህርት መርሀ ግብርን ላስተባበሩ የአካዳሚክ ኃላፊዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ በጀት ብር 247,500.00 አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣

- ለዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሾፌሮች ለመስክ ቆይታ በመደበኛ የቀን የውሎ አበል ላይ በተጨማሪ ለአል.ጋ በቀን ብር 100.00 ከውስጥ ገቢ ሂሳብ እየተደጎመ እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በ25/07/2005 በቃለ-ጉባኤ በወሰነው መሠረት በመከፈሉ በድምሩ ብር 272,786.19 ከመመሪያ ውጭ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣

2. <u>2007 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት፡-</u>
   - ከመደበኛ አበል በተጨማሪ ከዉስጥ ገቢ በቀን ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመስክ ቆይታ ለአል.ጋ እየተደጎመ እንዲከፈል በ02/08/2005 በቃለ-ጉባኤ በወሰነው መሠረት ሙሉ የቀን የውሎ አበል ከመደበኛ በጀት ላይ ከተወሰደ በኋላ በተጨማሪ ከዉስጥ ገቢ ሂሳብ ለአል.ጋ በሚል በድምሩ ብር 81,000.00 ከመመሪያ ውጪ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱንና ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገቢ አለመደረጉን፣
   - ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ውጪ ለሚሰጣቸው የማታ ትምህርት መርሃ ግብር የትምህርት ስልጠናዎች ላይ በማስተባበር ለሰሩ የአስተዳደር ሰራተኞች የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ብር 37,410.00 የትርፍ ሰዓት ተከፍሎ መገኘቱንና፤ ተመላሽ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያልተውሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.1.2 <u>ስጋት</u>፣

በኦዲት በሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት ዩኒቨርሲቲው የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ዘንድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን አይቻልም፡፡ የመንግሥት ገንዘብና ንብረትም እንዲመዘበር መንገድ ይከፍታል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት የሚያወጣቸው አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይከበሩ ይችላሉ፡፡

6.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም

በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የእርምት እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት እንዲቀርብ በድጋሚ እናሳስባለን።

6.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ምላሽ አልተሰጠም፡፡

በመጨረሻም ለተደረገው የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!